ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 286 ሰኔ 16 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## «ለአረንጓዴ ልማት ሽግግር ለሚያስፈልገው የገንዘብ ድጋፍ ጠንካራ ዘዴ መፍጠር ያስፈልጋል»

-ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- ወደ አረንጓዴ ልማት ሽግግር ለማድረግ ለሚያስፈልገው የገንዘብ ድጋፍ ጠንካራ ዘዴ መፍጠር እንደሚያስፈልግ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ «የ21ኛው ክፍለ ዘመን ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ የባለብዙ ወገን ልማት ባንኮችን ሞዴል ማሻሻል» በሚል ርዕስ በፈረንሳይ ፓሪስ በተዘጋጀው ውይይት ላይ እንደገለጹት፤ ወደ አረንጓዴ ልማት ሽግግር ለማድረግ ለሚያስፈልገው የገንዘብ ድጋፍ ጠንካራ ዘዴ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፈረንሳይ ፓሪስ በተካሄደው አዲስ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ስምምነት ጉባኤ ላይ አራት ነጥቦችን አንሥተው አጽንዖት ሰጥተዋል። ነጥቦቹም ከዚህ በፊት ቃል የተገቡ ስምምነቶችን መተግበር እንደሚያስፈልግ፤ የኮንሴሽናል ፋይናንስ አቅርቦትን


«ለአረንጓዴ ልማት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







## ‹‹የዓባይ ግድብ የትብብርና የጋራ የውሃ ሀብት ፍትሐዊ አጠቃቀም ተምሳሌት ነው››

አቶ ደመቀ መኮንን
- ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- የዓባይ ግድብ የትብብርና የጋራ የውሃ ሀብት ፍትሐዊ አጠቃቀም ተምሳሌት ነው ሲሉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን አስታወቁ፡፡

«በአዲሱ ዘመን የአፍሪካ ሀብት ለአፍሪካውያን ብልጽግና» በሚል መሪ ቃል በአፍሪካ ውስጥ የወሰን ተሻጋሪ የውሃ ሀብቶች ፍትሐዊና ምክንያታዊ በሆነ መልኩ አጠቃቀም ላይ ያተኮረ 2ኛው ‹‹አፍሪ ራን›› ከፍተኛ ኮንፈረንስ በትናንትናው ዕለት ተካሂዷል፡፡

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በኮንፈረንሱ ላይ እንደገለጹት፤ የዓባይ ግድብ ፍትሐዊ የውሃ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ከሚደረጉ ጥረቶች አንዱ ማሳያ ነው፡፡ የዓባይ ተፋሰስ አገራት የሚኒስትሮች ኮንፍረንስ በኢትዮጵያ መዘጋጀቱ አገራችን በዓባይ ተፋሰስ ላይ ፍትሐዊ ሥርዓት እንዲኖር



ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

ያላትን ፍላጎትና ቁርጠኝነት ይመሰክራል።

‹‹አፍሪ- ራን›› የጋራ ሀብቶቻችንን ለመጠቀምና የሚያጋጥሙንን ተግዳሮቶች ለመቋቋም የሚረዱን ጠቃሚ


‹‹የዓባይ ግድብ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## አገራዊ ምክክሩ በምክንያታዊነት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን አስፈላጊውን ድጋፍ እናደርጋለን

ልጅዓለም ፍቅሬ

አዲስ አበባ፡- የአገራዊ ምክክሩ በምክንያታዊነትና በእውቀት የተመሠረተ እንዲሆን አስፈላጊውን ድጋፍና ዕገዛ እንደሚያደርጉ የወላይታ ሶዶ፣ የባህር ዳርና የኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንቶች ተናገሩ፡፡

አገራዊ ምክክሩ ትልቅ ተስፋ የተጣለበትና እውቀትና ልምድን የሚጠይቅ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቶቹ፤ ምክክሩ ስኬታማ እንዲሆን ዩኒቨርሲቲዎች የማይተካ ሚና እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡

የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ፍሬው ተገኝ (ዶክተር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የአገራዊ ምክክሩ በእውቀት፣ በእውነትና በምክንያታዊነት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ዩኒቨርሲቲያቸው ሙያዊ ድጋፍ እንደሚያደርግ ተናግረዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች የእውቀትና የልምድ መገኛ በመሆናቸው ለአገራዊ ምክክሩ ትልቅ ግብዓት ማቅረብ ይችላሉ ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ዩኒቨርሲቲዎች የውይይት መድረኮች በማመቻቸት፣ ባለሙያን በማቅረብና ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት እንዲሁም የተለያዩ ሁነቶች


አገራዊ ምክክሩ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል












## አዲስ አበባን የኢንዱስትሪ ማዕከል ለማድረግ እየተሠራ ነው

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- አዲስ አበባ የዓለም ዲፕሎማቲክ መቀመጫ እንደሆነችው ሁሉ የኢንዱስትሪ ማዕከል ለማድረግ እየሠራን እንገኛለን ሲሉ የአዲስ አበባ ምክትል ከንቲባ እና የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ ገለጹ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ጃንጥራር ዓባይ፤ 12ኛው ዙር የአዲስ አበባ ኢንተርፕራይዞች የእውቅናና ሽግግር መርሐ ግብር ትናንት ሲካሄድ እንደተናገሩት፤ ከተማችን አዲስ አበባ የዓለም ዲፕሎማቲክ መቀመጫ እንደሆነችው ሁሉ የኢንዱስትሪ ማዕከል ለማድረግም እየሠራን እንገኛለን። ወደ ብልጽግና ለማምራት በሚደረገው ጥረት አስተዳደሩ የፈጠራ ባለቤቶችን በማበረታታት ላይ እንደሆነ ገልጸዋል።


አዲስ አበባን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# አረንጓዴው መሻገሪያ

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር በ2011 ዓ.ም ሐምሌ ወር ላይ ሲጀመር በመጀመሪያው ምዕራፍ በአራት ዓመታት ውስጥ 20 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል እቅድ ተይዞ ወደ ሥራ መገባቱ ይታወሳል።ይህንን ውጥን ከግብ ለማድረስ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ችግኞችን በመትከልና በመንከባከብ ሥራዬ ብለው ተያይዘውታል።ስለሆነም በመጀመሪያው ምዕራፍ በአገር አቀፍ ደረጃ 25 ቢሊዮን ችግኞች ተተክለዋል።የጽድቀት መጠኑም ከ80 በመቶ በላይ እንደሆነ ከግብርና ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

የአፈር መሸርሸር እንዳይኖር፣ የተፈጥሮ ሚዛኑ እንዲጠበቅ፣ የግብርና ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ብሎም ምቹ አካባቢን የመሻት እሳቤ ይሳካ ዘንድ መሻገሪያው አረንጓዴ ዐሻራ ነው።ኢትዮጵያ የጀመረችው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር የተራቆቱ መሬቶችን አረንጓዴ ካባን ከማጎናፀፉም በላይ ለጎረቤት አገራትም የሚገድ ጉዳይ ሆኗል።

የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ሲጀመር በብዛት በደን እና በመጤ ተክሎች ላይ ሲሠራ የቆየ ቢሆንም፤ ሃሳቡ እየሰፋ በመሄዱ አሁን ላይ ለአገር በቀልና ለምግብነት በሚውሉ ተክሎች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ይገኛል።የሚተከሉት የችግኝ ዓይነቶች ለከተማ ውበት፤ ለምግብነት እንዲሁም የተመናመነውን የደን ሽፋን እንዲያገግም ለማድረግ ወሳኝ ሚና አለው፡፡

የመጀመሪያው ዙር የአረንጓዴ ዐሻራ ትግበራ በእጥፍ ድርብ ድሎች ታጅቦ ተጠናቋል።የሁለተኛው ምዕራፍ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር በተያዘው ዓመት በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ሰኔ አንድ ቀን የንቅናቄ ሥራው ተጀምሯል።በማስጀመሪያው መርሐ ግብር ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደተናገሩት፤ በሁለተኛው ምዕራፍም 25 ቢሊዮን ችግኝ በመትከል በስምንት ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያን 50 ቢሊዮን ችግኝ ለማልበስ ዕቅድ ተይዟል፡፡

በአረንጓዴ ዐሻራ የለሙት ዛፎች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል ሲሉ ምሁራን ይናገራሉ።ባለፉት አራት ዓመታት ከተተከሉት 25 ቢሊዮን ችግኞች በትንሹ 30 በመቶ የሚሆነው እንኳን ቢጸድቅ ከዓመታት በኋላ እያንዳንዱ ዛፍ 200 ኪሎ ግራም ካርቦን ቢይዝ በአጠቃላይ በብዙ ሚሊዮን



ቶን የሚገመት ካርቦን ያጸዳል ይላሉ በብሔራዊ የካርቦን ልቀት ቅነሳ ፕሮግራም አስተባባሪ ዶክተር ይተብቱ ሞገስ።

አረንጓዴ ተክሎች የተቃጠለ እና ሙቀት አማቂ ጋዝን አየር ላይ ከመምጠጣቸው በተጨማሪ ኢትዮጵያ በስፋት በተራራ እና በገደሎች የተሸፈነች አገር በመሆኗ በዘላቂነት የሚጠበቅ ደን ያስፈልጋል የሚሉት ዶክተር ይተብቱ፤ በአገሪቱ ደኖች በመመናመናቸው በክረምት ጎርፍ፤ በበጋ የውሃ እጥረት ያስቸግራል።በመሆኑም ግድቦች በንጹህ ውሃ እንዲሞሉ ዝናብን ለማጠናከር፣ ድርቅን ለመከላከል ዛፎች መኖራቸው ወሳኝ ነው ብለዋል።ከሚተከሉት የፍራፍሬ እና ምግብ ነክ ችግኞች የሚገኘው ምርት የአገሪቱን ኢኮኖሚ ከፍ እንደሚያደርገውም የካርቦን ልቀት ቅነሳ ፕሮራም አስተባባሪው ተናግረዋል፡፡

ዶክተር ይተብቱ አክለውም፤ ኢትዮጵያ የውሃ ማማ እንደመሆኗ የቀጣናው አገራት በአገሪቱ ውሃ ላይ ጥገኛ ናቸው።በመሆኑም የኢትዮጵያ የደን ልማት ለቀጣናው ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ግብርና እና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ ፕሮፌሰር ይሄነው ገብረሥላሴ በበኩላቸው፤ እጽዋት ከአካባቢ የሚለቀቀውን ካርቦንዳይ ኦክሳይድ በመምጠጥ፤ በምላሹ ኦክስጂንን ስለሚለቁ ለአየር ንብረት ለውጥ ሚናቸው ጉልህ ነው ሲሉ ይገልፃሉ።

ኢትዮጵያ በስፋት ተራራማ አካባቢዎች የሚገኙባት ስለሆነች ከከፍታ ቦታዎች ዝናብ በሚዘንብበት ወቅት ጎርፍን ያስከትላል፤ ከፍተኛ የሆነ የአፈር መሸርሸርም ያጋጥማል።መንግሥት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐግብርን ማስጀመሩ እና እጽዋቶች በስፋት መተከላቸው እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ ጠቃሚ ነው ብለዋል፡፡

የአረንጓዴ ዐሻራ ከኢኮኖሚ አንጻር ያለውን ጠቀሜታ ያነሱት ፕሮፌሰር ይሄነው፤ ለእጽዋቶቹ መትከያ ጉድጓድ በመቆፈር፣ በመትከል እና የተተከሉትን እጽዋቶች በመንከባብ በርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል ሊፈጥርላቸው እንደሚችል አስገንዝበው፤ እጽዋቶቹ ለፍሬ ሲደርሱ ለምግብነት፣ ለግንባታ ሥራዎች፣ ለማር ምርት፣ ለእጣን፣ ለማገዶ እና ለተለያዩ ነገሮች ስለሚውሉ ለአገሪቱ ኢኮኖሚ ሚናቸው የጎላ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ጎረቤት አገራት በረሃማ መሆናቸውን ያነሱት ፕሮፌሰር ይሄነው፤ በአካባቢዎቹ በንፋስ አማካኝነት በከፍተኛ ሁኔታ የአፈር መከላት እንደሚያጋጥም አንስተው፤ አንዳንዴ ከሱዳን የሚነሳው አቧራ ወደባህርዳር እየመጣ የአውሮፕላን በረራዎችን የሚያስተጓጉልበት አጋጣሚ እንዳለ አስታውሰዋል።ለዚህም ዛፍ መትከል እና መንከባከብ ጠቀሜታው ዘርፈ ብዙ መሆኑን አስገንዝበዋል።

# አገልግሎቱ የንባብ ክበባትን በማቋቋም የአንባቢን ቁጥር ለማሳደግ እየሠራ ነው

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመ ጻሕ ፍት አገልግሎት በየአመቱ ከስ ድስት እስከ 10 የሚደርሱ የንባብ ክበባትን በማቋቋም የንባብ ባህልን ለማሳደግ እየ ሠራ መሆኑን አስታወቀ።

ኅብረተሰቡን በማስተ ባበር በየክልሉ ደረጃቸውን የጠበቁ ቤተመጻሕፍትን በማስፋፋት የአንባቢያንን ቁጥር ማሳደግ እንደሚገባም አስታውቋል።

ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድር ጅት ጋር ቆይታ ያደረጉት በኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት አገልግሎት የአብያተ መጻሕፍት አገልግሎት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ያሬድ ተፈራ እንደገለጹት፤ ደረጃቸውን የጠበቁ ቤተ መጻሕፍት መበራከት የአንባቢንን ቁጥር እንዲጨምር አስተዋጽኦ አለው። መንግሥት ኅብረተሰቡን በማስተባበር ቤተ መጻሕፍትን በየአካባቢው እንዲሰፉ ማድረግ ይኖርበታል።

ንባብ የሰዎችን ሁለንተናዊ ማንነት የሚቀርጽ በመሆኑ የንባብ ባህላችን ማደግ አለበት ያሉት አቶ ያሬድ፤ የመጻሕፍት ህትመት ዋጋ መጨመርና በየአካባቢው ደረጃቸውን የጠበቁ ቤተ መጻሕፍት አለመኖራቸው የንባብ ባህል እንዳያድግ እንዳደረገ ተናግረዋል።

የአብያተ መጻሕፍት አገልግሎት የአንባብያንን ቁጥርን ለመጨመርም ከ2006 አመተ-ምህረት ጀምሮ በየዓመቱ ከስድስት እስከ 10 የሚደርሱ የንባብ ክበባትን በትምህርት ተቋማት ሲያቋቁም እንደቆየ ጠቁመው፤ በዚህም ታዋቂ ደራሲያን ለመምህራን ስልጠናዎችን መስጠታቸውን ተናግረዋል።

ስልጠናዎቹም መምህራን ለተማሪዎቻቸው መጻሕፍትን እንዴት ማንበብ እንዳለባቸውና እንዴት መቃኘት እንደሚችሉ ግንዛቤን ያስጨበጠ መሆኑን አብራርተዋል። በተያዘው ዓመትም በወላይታ፤ ዱራሜና ሞጣ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ተመሳሳይ ሥራዎችን እንደሠሩ ተናግረዋል።

የዲጂታል ዓለሙ ሰዎች በቀላሉ የሚፈልጉትን መረጃዎች ማግኘት እንዲችሉ የሚያደርግ ቢሆንም ሰዎች ግን በዲጂታል መገናኛው ቁንጽል ነገሮችን ወይም እውቀቶችን ለማግኘት እንደሚጠቀሙበት አብራርተዋል። የዲጂታል ዓለሙን በአግባቡ መጠቀም ቢቻል በርካታ እውቀት ማግኘት የሚቻልበት መሆኑን ገልጸው አንባቢ ትውልድ ለማፍራት አስተዋፅዖ እንደሚኖረው ተናግረዋል።

የቤተ መጻሕፍት ባለሙያዎች አስፈላጊና እውነተኛ መረጃዎች የያዙ መጻሕፍትን በአንባቢያን ዕድሜ እና የእውቀት ደረጃ በመምረጥ መጻሕፍት እንዲነበብ ማድረግ እንዳለባቸው ጠቁመው፤ አንባቢ ትውልድን ለመፍጠርም በንባብ ዙሪያ መምህራን፤ ወላጆችና ባለድርሻ አካላት ውይይቶችንና የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት እንዳለባቸው ተናግረዋል።

# ብልጽግናን ለማረጋገጥ በቴክኒክና ሙያ ዘርፉ ላይ ተጨባጭ ውጤት ማምጣት ያስፈልጋል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ብልጽግናን ለማረጋገጥና ያደጉ አገራት የደረሱበት ደረጃ ለመድረስ በቴክኒክና ሙያ ዘርፉ ላይ ውጤት ማምጣት እንደሚያስፈልግ ተገለጸ።«ሙያና ክህሎት ለስኬት» በሚል መሪ ቃል የተካሄደው 13ኛው ቴክኒክና ሙያ ሳምንት የእውቅና እና የማጠቃለያ ፕሮግራም ትናንት ተከናውኗል።

የእውቅናና የማጠቃለያ ፕሮግራም ትናንት በተካሄደበት ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ማሾ ኦላና እንደገለጹት፤ አገራት የተለወጡትና አሁን ለደረሱበት ደረጃ ትልቁን ሚና የተጫወተው የቴክኖሎጂ እድገት ነው።በአዲስ አበባም ቢሮው በአዲስ ከተደራጀ ወዲህ በቴክኖሎጂው ዘርፍ አዳዲስ ለውጦች እያስመዘገበ ነው።

እንደ አቶ ማሾ ገለጻ፤ ዘርፉ ለአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ሳይሆን ለአገር የሚጠቅም ነው።ቴክኖሎጂ በመፍጠር አገርን ተወዳዳሪ የሚያደርግ ሥራ መሥራት ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም።እውቅናው አሁን ለተገኘው ውጤት ብቻ ሳይሆን ለቀጣይ ሥራዎች ወኔ የሚሰጥ ጭምር ነው።

ዘርፉ በርካታ ፍላጎቶች ያሉበት በመሆኑ ሰፊ ሥራዎችን ማከናወን ይቻላል ያሉት አቶ ማሾ፤ ተግቶ በመሥራት አዲስ አበባን በዘርፉ ተወዳዳሪ ከተማ ማድረግ ያስፈልጋል።አገራት የደረሱበት ደረጃ ለመድረስ በቴክኒክና ሙያ ዘርፉ ውጤት ማስመዝገብን ይጠይቃል።ለዚህም ሁሉም የዘርፉ ተዋናይ ጠንክሮ መሥራት እንደሚገባው አሳስበዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሀቢባ ሲራጅ በበኩላቸው ዘርፉ በውጤት ተኮር ስልጠና በመታገዝ ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን ብቁ የሰው ኃይል በማፍራት



እና ኢንተርፕራይዞች የምርት ጥራታቸውን በማሻሻል ወደ ኢንዱስትሪው እንዲሸጋገሩ ለማስቻል በትኩረት እየተሠራ ነው ብለዋል።

ኢንተርፕራይዞች የምርት ጥራታቸውን ለማሳደግ ቴክኖሎጂዎችን በመቅዳት ተወዳዳሪን ለመሆን ሊሠሩ ይገባል።ወደ ኢንዱስትሪው ለመሸጋገርም በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ትኩረት ሰጥተው መሥራት ይኖርባቸዋል ነው ያሉት፡፡

የቴክኒክና ሙያ ሳምንት እንደ አገር ተኪ ምርቶች ለማምረት የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን ለማፍለቅ ትልቅ መነሳሳት የሚፈጥር ነው ያሉት ቢሮ ኃላፊዋ፣ በቀጣይም ዘርፉ ውጤታማ እንዲሆን በየደረጃው ያሉ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች፣ ኢንተርፕራይዞች፣ አምራቾችና ሌሎች የዘርፉ ባለድርሻ አካላት መሥራት እንደሚጠበቅባቸውም ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ፣ አቶ መኩብብ ወልደሃና በበኩላቸው፤ የእውቅና መርሃ ግብሩ በተለያዩ ውድድሮች አሸንፈው ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ደረጃ የወጡ አሰልጣኞች፣ የኢንተርፕራዝ አንቀሳቃሾችና ሌሎች ተወዳዳሪዎች እውቅና ተበርክቶላቸዋል።

ሙያና ክህሎት ለስኬት በሚል መሪ ቃል ከሚያዝያ 26 እስከ 30 2015 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል መከበሩን ያስታወሱት አቶ መኩብብ፤ ዋና አላማውም በኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች፣ የቴክኖሎጂ ባለቤቶች፣ በሙያና ቴክኒክ ኮሌጆች መካከል የእርስ በእርስ ውድድር የሚፈጥር መሆኑን ገልጸዋል።

በማጠቃለያ መርሃ ግብሩ በተለያዩ ዘርፎች ከአንድ እስከ ሦስተኛ ደረጃ ለወጡ 110 ተወዳዳሪዎች፣ አሰልጣኞችና ዳኞች የእውቅና፣ የማበረታቻ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

እውቅና የተሰጣቸው አሰልጣኞች፣ ኮሌጆች፣ የፈጠራ ባለቤቶች በቀጣይም የበለጠ ውጤት ለማስመዝገብ እንደሚሠሩ ገልጸዋል።

# በክልሉ በመጪው ዓመት በቴሌ ብር 130 ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዷል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል በመጪው ዓመት በቴሌ ብር 130 ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ መታቀዱን የክልሉ ገቢዎች ቢሮ አስታወቀ።

ግብርን በቴሌ ብር ለመሰብሰብ የሚያስችል ስምምነት የኢትዮ ቴሌ ኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሪት ፍሬህይወት ታምሩና በምክትል ፕሬዚዳንት ማዕረግ የኦሮሚያ ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ መስከረም ደበበ በትናንትናው ዕለት ተፈራርመዋል።

በምክትል ፕሬዚዳንት ማዕረግ የኦሮሚያ ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ በስምምነቱ ወቅት እንደገለጹት፤ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የክልሉን ወጪ በክልሉ ገቢ ለመሸፈን የሚያስችል ግብርን በቴክኖሎጂና በሰለጠነ የሰው ኃይል ለመሰብሰብ እየተሠራ ነው። በዚህም በቀጣይ ዓመት 130 ቢሊዮን ብር ገቢ በቴሌ ብር አማካኝነት ለመሰብሰብ ታቅዷል።

እንደ ወይዘሮ መስከረም ገለጻ፤ ክልሉ አገራዊ የግብር እቅዱን ለማሳካት እየሠራ ይገኛል። በዚህም የታክስ አሰባሰብ ሥርዓቱን ዘመናዊና ምቹ በማድረግ በቴሌ ብር ለመሰብሰብ ከኢትዮ ቴሌ ኮም ጋር የመግባቢያ ሰነድ ተፈርሟል።

በኦሮሚያ ክልል ግብር ከጊዜ ወደ ጊዜ በማደግ



ላይ ነው ያሉት ኃላፊዋ፤ በ2010 ዓ.ም 16 ቢሊዮን ብር መሰብሰቡን አስታውሰዋል። በተለይም በ2015 ዓ.ም 71 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር መሰብሰብ የተቻለ መሆኑን ጠቅሰው፤ በ2016 ዓ.ም 130 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ መታቀዱን ገልጸዋል።

ለዜጎች ምቹ የሆነች አገርን ለመገንባት የኢኮኖሚው ዘርፍ የሚያመነጨውን ገቢ መሰብሰብ ተገቢ መሆኑን ጠቅሰው፤ የአሰባሰብ ሥርዓት ማዘመን አማራጭ የሌለው ተግባር ነው ብለዋል።

በክልሉ የታክስ አሰባሰብን በማዘመን ቀልጣፋ፣ ተደራሽና ከብልሹ አሠራር የጸዳ ለማድረግ እየተሠራ ነው። በዚህም ከቴሌ ብር ጋር የአሠራር ሥርዓቱን በማቀናጀት የገቢ አሰባሰቡን ወደ ዲጂታል ዓለም በመቀላቀል የገቢ ዘርፉን ለማዘመን በመሥራት ላይ መሆኑን ተናግረዋል።

የኢትዮ ቴሌ ኮም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሪት ፍሬህይወት ታምሩ በበኩላቸው በኢት ቴሌ ኮም ቴሌ ብር ተግባራዊ ከተደረገ ጊዜ ጀምሮ 34 ሚሊዮን ደንበኞችን አፍርቷል። ይህም ዜጎች ካሉበት ቦታ ሆነው ግብር የሚከፍሉበትና ጊዜያቸውን ለመቆጠብ የሚያስችል ነው።

ቴሌ ብር በክልሉ የሚገኙ ግብር ከፋዮች ከየትኛውም ቦታ በቀላሉ በቴሌ ብር ለመክፈል ያስችላል ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፤ አገልግሎቱን ተደራሽ በማድረግ የዲጂታል ኢትዮጵያን ራዕይ እውን ለማድረግ በመሥራት ላይ ነው ብለዋል።

ደንበኞች የገቢ ግብርና የቀረጥ ክፍያቸውን ቀላል፣ ፈጣንና አስተማማኝ በሆነው ቴሌ ብር እንዲከፍሉ ተግባራዊ መደረጉን ጠቅሰው፤ ክልሉ የግብር አሰባሰብ ሥርዓቱን በዲጂታል ሥርዓት (ሲስተም) የተደገፈ በማድረግ የዘመነ የግብር አሰባሰብ ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል መሆኑን አመላክተዋል።

ቴሌ ብር ለደንበኞች ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት የክፍያ ደረሰኝ ማጭበርበርን ለማስወገድና የመልካም አስተዳደርን ለማስፈን ያስችላል። በዚህም ዜጎች በቀላሉ የቴሌ ብር የሞባይል መተግበሪያ ወይም *127# አጭር ቁጥርን በመክፈል የክፍያ ማረጋገጫ ደረሰኝ ወዲያውኑ ለማግኘት እንደሚያስችል ገልጸዋል።

የዲጂታል ክፍያ ሥርዓቱ ተግባራዊ ከመደረጉ አስቀድሞ በቂ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መሠራቱን ገልጸው፤ ለሠራተኞችና ለግብር ከፋዮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መሰጠቱን አስረድተዋል።

# ኤምባሲው የኢትዮጵያን ሚዲያዎች ለማጠናከር 57 ሚሊዮን ብር መደበ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ኤምባሲው የኢትዮጵያን ሚዲያዎች ለማጠናከር 57 ሚሊዮን ብር መመደቡን በኢትዮጵያ የፈረንሳይ ኤምባሲ አስታውቋል።

የፈረንሳይ ኤምባሲ ለኢትዮጵያ ሚዲያ የድጋፍ ፕሮግራም በትናንትናው ዕለት ባስጀመረበት ወቅት በኢትዮጵያ የፈረንሳይ ኤምባሲ አምባሳደር ረሚ ማሪሾ በድጋፍ መርሐ ግብሩ ላይ ተገኝተው እንደገለጹት፤ የፈረንሳይ ኤምባሲ ለኢትዮጵያ ሚዲያ ድጋፍ ፕሮግራም የ944 ሺህ ዩሮ ወይም የ57 ሚሊዮን ብር በጀት መድቧል። ፕሮግራሙ የአገሪቱ ኦዲዮ ቪዥዋል የመረጃ ቋትን የማዘመንና ብሔራዊ ተነሳሽነት በመደገፍ ሚዲያዎችን ለማጠናከር ጉልህ ሚና አለው።ፕሮግራሙ ሚዲያዎች ሕጋዊነታቸውን ጠብቀው አገልግሎት እንዲሰጡ ያለመ የዴሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ ግንባታ አካል ነው ብለዋል፡፡

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፤ በቀጣዮቹ ሁለት ዓመታት የሚቆየው ይህ ፕሮግራም ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ምክር ቤት እና ከኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ጋር በመሆን የሚሠራ ይሆናል። በተጨማሪም ሁለት የፈረንሳይ ድርጅቶች ካናል ፍራንስ ኢንተናሽናል (CFI) እና የኦዲዮቪዥዋል ብሔራዊ ተቋም (INA) የኢትዮጵያ ሚዲያን ለማገዝ በአጋርነት ይሠራሉ።

ፈረንሳይ በዚህ አዲስ የአጋርነት ፕሮግራም በቁርጠኝነት የምትሠራ ሲሆን በአገሪቱ መረጋጋትና ዘላቂ ሰላም እንዲኖር የበኩሏን አስተዋጽኦ ታደርጋለች ያሉት አምባሳደር ረሚ ማሪሾ፤ በኢትዮጵያ ያለው የማኅበራዊ ትስስር እንዲጎለብትም የሚዲያዎችን አቅም በማጎልበት ብዝኃነት ያለው፣ እምነት የሚጣልበት እና አካታች መረጃ እንዲኖር ታግዛለች ብለዋል።

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ በፈረንሳይ መንግሥትና በዚህ ፕሮግራም በታቀፉት አጋሮች የሚካሄደው ይህ መርሐ ግብር ሦስት ክፍሎችን ይዟል። የመጀመሪያው ካናል ፍራንስ ኢንተርናሽናል የሚዲያ ስልጠና ለማስፈጸም ከኢትዮጵያ ሚዲያ ምክር ቤት ጋር በቅርበት ይሠራል።ስልጠናውም በመላው ኢትዮጵያ በጥላቻ ንግግርና ሃሰተኛ መረጃን መከላከል እንዲሁም ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች ስለሚኖር ጋዜጠኝነት ላይ ያተኩራል፡፡

በሁለተኛው ለመገናኛ ብዙኃን ምክር ቤቱ



አምባሳደር ረሚ ማሪሾ



አቶ አማረ አረጋዊ

የግልግል ዳኝነት አካል ድጋፍ ይሰጣል።ሦስተኛው ክፍል ፕሮግራሙ ኢትዮጵያዊ ቅርስን የመንከባከብን አስፈላጊ ገጽታ ይመለከታል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ አማረ አረጋዊ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ምክር ቤት ከፈረንሳይ ኤምባሲ ጋር ሲሠራ የመጀመሪያው በመሆኑ የፕሬስ ነፃነት በማረጋገጥ በኩል ትልቅ ጥቅም ያስገኛል።በኢትዮጵያ ውስጥ አንዳንድ ኃላፊነት የጎደላቸው ሚዲያዎች የሃሰት ዜናዎችንና የጥላቻ ንግግሮችን ያሰራጫሉ።ይህም ጋዜጠኝነት እና የሙብት ተሟጋችነት እየተደበላለቀ መምጣቱን ያሳያል ብለዋል፡፡

ፕሬዚዳንቱ የፈረንሳይ ኤምባሲ ድጋፉን በትክክለኛው ጊዜ በማድረጉ የተሰማቸውን ደስታ ገልጸው፤ ድጋፉም የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃንና የሙያተኞቹን አቅም በማሳደግ ረገድ ትልቅ ሚና እንደሚኖረው ገልጸዋል፡፡

# «አንጻራዊው ሰላም ወደተሻለ ደረጃ እንዲደርስ ፖለቲካዊ ስክነት ያስፈልጋል»

-የተፎካካሪ ፓርቲ አመራሮች

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሁለት ዓመታት ኢትዮጵያ ከነበረችበት የውጭ ጫና እና የአገር ውስጥ ውጥረት አንጻር አሁን የመጣው አንጻራዊ ሰላም ወደተሻለ ደረጃ እንዲደርስ የፖለቲካ ስክነት ሊኖር ይገባል ሲሉ የተፎካካሪ ፓርቲ አባላት ገለጹ፡፡

የእናት ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ አባልና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ዳዊት ብርሃኑ፤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ጊዜያት ኢትዮጵያ ከነበረችበት ውጥረት አንጻር አሁን የመጣው አንጻራዊ ሰላም የተሻለ ደረጃ እንዲደርስ በሁሉም ሕዝብና ልሂቃን ዘንድ የፖለቲካ መረጋጋት ሊኖር ይገባል፡፡

አቶ ዳዊት እንደተናገሩት፤ ችግሮች ሲፈጠሩ ስሜታዊ የሆኑ ንግግሮችና ርምጃዎችን ከመውሰድ ይልቅ፤ የተፈጠሩ ችግሮችን ወደጠረጴዛ ዙሪያ አምጥቶ መወያየት እንዲሁም የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ለማስቀመጥ መሞከር የተሻለ ነው።

ፖለቲካዊ ስክነት የሚፈጥሩ አካላት ሲበዙ በጋራ ተቀምጦ መወያየትና መመካከሩ ውጤታማ ይሆናል ሲሉ አስረድተዋል።

አቶ ዳዊት እንዳስታወቁት፤ ግጭት ሊያስከትሉ የሚችሉ አለመግባባቶች ሲከሰቱ በሰከነ መንገድና በሰለጠነ የሀሳብ ጉልብትና ለመፍታት ብዙ ርቀቶችን መጓዝ ያስፈልጋል።

የተሻለ ሰላም ለማምጣት መንግሥት ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር ይበልጥ ተቀራርቦ መወያየት አለበት ያሉት አቶ ዳዊት፤ ይህም የውጭ ጫናዎችንና የአገር ውስጥ ችግሮችን በጋራ ለመመከት እና የአገር ውስጥ ችግሮችን በጋራ ለመመከት አቅም ይፈጥራልም ብለዋል።

እንደ አቶ ዳዊት ገለጻ፤ ግለሰቦችንና ተቋማትን ከመፈረጅ አስቀድሞ በጉዳዩ ላይ ጥናቶች እና ውይይቶች በማድረግ ለችግሮች መፍትሔ ማበጀት ይገባል።

በተጨማሪም በየዘርፉ የሚገኙ ምሁራን በአገሪቱ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመመልከት የራሳቸውን ዕውቀት ተጠቅመው ተገቢውን አቅጣጫ ሊጠቁሙ ይገባል ሲሉ ሃሳብ ሰጥተዋል።

የአፋር ሕዝብ ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ ሙሳ አደም በበኩላቸው፤ አሁን የመጣው አንጻራዊ ሰላም ወደተሻለ ደረጃ እንዲደርስ የፖለቲካ አመራሮች ሰላምን ከማምጣት አንጻር በሰከነ መንገድ መንቀሳቀስና የውይይት ባህልን ማዳበር ይኖርባቸዋል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ማህበራዊ ሚዲያ አንቀሳቃሾችም ሕዝብን ወደግጭት ከሚመሩ ጉዳዮች ተቆጥበው ነገሮችን በአወንታዊ



አቶ ዳዊት ብርሃኑ



አቶ ሙሳ አደም

መልኩ በመመልከት ምክንያታዊነትን መሠረት ያደረጉ መረጃዎችን ማሰራጨት ይጠበቅባቸዋልም ብለዋል።

የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሀሳብን በሀሳብ ለመርታት መሥራት እንዳለባቸው የተናገሩት ሊቀመንበሩ፤ ፓርቲዎች ለተከታዮቻቸውና ለአባሎቻቸው የሚያስተላልፉት መልዕክት የአገርን ሉአላዊነት በማይጋፋ መልኩ ሚዛኑን የጠበቀና ሰላምን የሚያረጋግጥ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው ሲሉ ተናግረዋል።

ኅብረተሰቡም ከፖለቲከኞችም ሆነ ከሌሎች አካላት የሚደርሱ መረጃዎችን አገናዝቦ በጥልቀት መመርመር እና በሰላም ጉዳይ ይበልጥ መሥራት እንዳለበት ገልጸዋል።

የአንዳችን ለቅሶ ለአንዳችን ደስታ መሆን የለበትም ያሉት አቶ ሙሳ፤ እንደ አንድ አገር ዜጋ በመረዳዳትና ሰላምን በሚያመጡ ጉዳዮች ላይ በጋራ በመሥራት የሕዝቡን ችግር መፍታት ይገባል ብለዋል፡፡



# በዞኑ ከሮዝመሪ ምርት ከሁለት ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኘ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ክልል ስልጤ ዞን ከሮዝመሪ ምርት ሁለት ሚሊዮን 621 ሺህ ዶላር ገቢ ማግኘት መቻሉን የዞኑ ግብርና መምሪያ አስታወቀ፡፡

በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የስልጤ ዞን ምክትል አስተዳዳሪና ግብርና ልማት መምሪያ ኃላፊ አቶ ሙርሰል አማን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2014/15 የምርት ዘመን ከተመረተው 49 ሺህ 550 ኩንታል ምርት ውስጥ 49 ሺህ 365 ኩንታል ምርት ለማዕከላዊ ገበያ ቀርቧል፡፡

ለማዕከላዊ ገበያ ከተላከው ምርት ውስጥም 13 ሺህ 799 ኩንታል ወደ ውጪ በመላክ ከሁለት ሚሊዮን 621 ሺህ ዶላር በላይ ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡

በስልጤ ዞን የሮዝመሪ ልማት በሦስት ወረዳ ይለማ ከነበረበት ወደ 10 ወረዳና ወደ ሦስት ከተማ አስተዳደር እየለማና እየተስፋፋ ይገኛል ያሉት ኃላፊው፤ ባለፈው የምርት ዘመን በሮዝመሪ የለማው ሁለት ሺህ ሄክታር ሲሆን ዘንድሮ የእርሻ መጠኑ በአንድ ሺህ ሄክታር እንዲጨምር ማድረግ ተችሏል ብለዋል፡፡

በቀጣይም በዘንድሮ ዓመት የለማውን ሦስት ሺህ 82 ሄክታር ወደ አራት ሺህ 760 ሄክታር ለማድረስ የንቅናቄ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

እንደ አቶ ሙርሰል ገለጻ፤ የሮዝመሪ ቅመምን በስፋት በመሥራት የአገር ውስጥ አቅርቦትና ወደ ውጭ የመላክ እንቅስቃሴዎች እያደጉ መጥተዋል፡፡ ከሮዝመሪ በተጨማሪ በሌሎች አዋጭ በሆኑ መድኃኒታማና መዓዛማ ቅመሞች በተለይ ላቫንደር ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ይገኛል፡፡

የሮዝመሪ የአካባቢ ዋጋ በኪሎ ግራም እስከ 70 ብር እየተሸጠ ሲሆን ዋጋው የመጨመርና የመውረድ ሁኔታዎች የሚታይ በመሆኑ በቀጣይ የገበያ ትስስሩ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራልም ብለዋል፡፡

# አዲስ አበባን የኢንዱስትሪ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

አዲስ አበባ የጀመረችው ሁሉን አቀፍ የለውጥ ጉዞ የሚሰምረው ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ሲቻል ነው ያሉት አቶ ጃንጥራር፤ ዜጎች በጥረት ማደግን የኑሮ መመሪያቸው ማድረግ እንዳለባቸው ጠቅሰዋል።

ከተማ አስተዳደሩ ሥራን በማበረታታትና በመደገፍ እንዲሁም የፋይናንስ አቅርቦትን በማመቻቸት፤ የመሥሪያና የመሸጫ ቦታዎችን በማቅረብ፤ አጫጭር የሙያ ሥልጠናዎችን በመስጠትና የካፒታል ሊዝ ፋይናንስ በማድረግ ሥራ ፈጣሪዎችን እየደገፈ መሆኑን አስታውቀዋል። በዚህም ከትንሽ ሥራ ተነስተው ያደጉ በርካቶች እንደሆኑ ተናግረዋል።

አቶ ጃንጥራር እንዳሉት፤ ትልልቅ ኢንዱስትሪዎች በድንገት ሊያድጉ አይችሉም፣ በምኞትና በተስፋም የሚገኙ አይደሉም። ከተማዋን የኢንዱስትሪ ማዕከል እናደርጋለን ሲባል የፈጠራ ባለቤቶችን በማበረታታት፤ የዛሬ ጥቃቅንና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን ተግዳሮቶቻቸውን በመፍታት ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ እንዲሸጋገሩ በማስቻል ነው።

በ12ኛው ዙር ሽግግር መርሐ ግብርም 469 ወደ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝና 12ቱ ደግሞ ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ በጠቅላላው 481 ኢንተርፕራይዞች ወደ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች መሸጋገር መቻላቸውን ገልጸዋል።

በሁሉም የእድገት ዘርፎች ሽግግር ያደረጉ ኢንተርፕራይዞች የከተማዋን የዋጋ ንረት በመከላከል ረገድ አዎንታዊ ሚና እንዲወጡም አቶ ጃንጥራር ጥሪ አቅርበዋል።

በቢሮ ኃላፊ ደረጃ የኢንተርፕራይዝ ድጋፍ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ሚኪያስ ሙሉጌታ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ ውስን የሆነውን የተፈጥሮ ሀብትና የካፒታል ጸጋውን በመጠቀም ፍትሃዊ ተጠቃሚነቷን ለማረጋገጥ የሥራ ዕድል ፈጠራ ፖሊሲና ስትራቴጂ ነድፋ ወደ ትግበራ ከገባች ሁለት አስርት አመታትን እያስቆጠረች መሆኗን ገልጸዋል። በዚህም ዜጎች በግል፣ በማህበርና በኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው የታላላቅ አምራች ኢንዱስትሪ ባለቤት እስከ መሆን መድረሳቸውንም ጠቅሰዋል።

በከተማዋ በአገልግሎት፣ በንግድ፣ በኮንስትራክሽን፣ በማኑፋክቸሪንና በከተማ ግብርና በኢንተርፕራይዝ ተደራጅተው ጥሪት ያፈሩ ዜጎችም በርካቶች መሆናቸውን አቶ ሚኪያስ ገልጸዋል።

ወደ ባለጸጋነት የተሸጋገሩ ሥራ ፈጣሪዎች ዋነኛ ምስጢር ከመንግሥት ያገኙት ድጋፍ ሳይሆን ጥረትን ከውጤታማነት ጋር በማጣመራቸው እንደሆነ ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ብልጽግና ፓርቲ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሞገስ ባልቻ፤ በኢኮኖሚው ዘርፍ ያለው የዓለም ነባራዊ ሁኔታ እንደሚያሳየው እድገት የሚገኘው ከትናንሽ ኢንተርፕራይዞች በመጀመር እንደሆነ ጠቅሰው፤ ተመራቂ ኢንተርፕራይዞች በውጤታማነት በመሥራት የላቀውን ማሰብ እንዳለባቸው አስገንዝበዋል። የበለጠ የሥራ ፈጠራ በማከልና ምርታቸውን ለውጭ ገበያ ለማቅረብና የሥራ ዕድል ወደ መፍጠር መሸጋገር አለባቸው ብለዋል። ለዚህም የከተማ አስተዳደሩ ድጋፍ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

# አገራዊ ምክክሩ ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

በማዘጋጀት ረገድ ሚናችንን መወጣት ይጠበቅብ ናል ነው ያሉት፡፡

እንደ ዶክተር ፍሬው ገለጻ፤ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲም በአገራዊ ምክክሩ የዩኒቨርሲቲዎች ሚና ምን መሆን አለበት በሚል አውደ ጥናት ቀርቦ ሰፊ ውይይት ተደርጎበታል።ዩኒቨርሲቲው በሰነድ የተደገፈ ለአገራዊ ምክክሩ ግብዓት በማቅረብ ኃላፊነቱን ተቀብሎ ተግባራትን እያከናወነ ነው፡፡

ዩኒቨርሲቲዎችና የምክክር ኮሚሽኑ በጋራ መሥራት ከቻሉ በአጭር ጊዜ የሚፈለገውን አገራዊ መግባባት ማምጣት እንደሚቻልም ተናግረዋል፡፡

ቀደም ባሉት ጊዜያት የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር ባደረገው ምክክር ከዩኒቨርሲቲዎች ምን እንደሚጠበቅ በግልጽ ታውቆ ወደ ተግባር መግባቱን ያስታወሱት ዶክተር ፍሬው፤ የአገራዊ ምክክሩ በእውቀት ላይ የተመሠረተ በማድረግ አኳያ ዩኒቨርሲቲዎች አይተኬ ሚና አላቸው ብለዋል፡፡

የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ታከለ ታደሰ በበኩላቸው፤ ምክክሩ በጥናትና ምርምር እንዲሁም በእውቀት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች በሰው ኃይል ልማት ሰፊ ሀብት አላቸው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ መድረኮችን ከማዘጋጀትና



ዶክተር ፍሬው ተገኝ

ከመምራት እንዲሁም የሃሳብ የበላይነት በኅብረተሰቡ ዘንድ ከማስረጽ አንጻር ሚናቸው ከፍተኛ ነው ብለዋል፡፡

እንደ ፕሮፌሰር ታከለ ገለጻ፤ ለአገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት ከዚህ በፊት በአገረ መንግሥት ግንባታ የምሁራን ሚና በሚል በተዘጋጀው መድረክ እና ምሁራን ተሳትፈው ያጠኑት የፖሊሲና ጥናት ጥሩ ማሳያ ናቸው።ዩኒቨርሲቲዎች ትንሿ ኢትዮጵያ በመሆናቸው የምክክር መድረኩ እንዲሳካ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

በአገራዊ ምክክሩ አገር በቀል የግጭት አፈታት ሥርዓትና የተግባቦት ልምዶች መካተት አለባቸው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ አውዱ ቢለያይም በዚህ ጉዳይ የተለያዩ አገራት ውጤታማ ሆነዋል።በኢትዮጵያ አውድ አካታች የሆነ የምክክር መድረክ



ፕሮፌሰር ታከለ ታደሰ

ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

የኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ብርሃነመስቀል ጠና (ዶክተር) በበኩላቸው ለአገራዊ ምክክሩ ስኬት ዩኒቨርሲቲዎች ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው አመልክተው፤ ለምክክሩ ቅድመ ሁኔታዎች ከማመቻቸት፣ ግብዓት የሚሆኑ ሃሳቦችን ከማቅረብ እና ሙያዊ ድጋፍ ከማድረግ አንጻር ከፍተኛ ሚና አላቸው ብለዋል፡፡

የምክክር ኮሚሽኑ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በቅርበት መሥራት እንዳለበት የጠቆሙት ዶክተር ብርሃነመስቀል፤ የአገራዊ ምክክሩ የተሻለ ውጤት እንዲያመጣ ዩኒቨርሲቲው ድጋፍ እንደሚያደርግም ተናግረዋል፡፡



ብርሃነመስቀል ጠና (ዶክተር)

እንደ ዶክተር ብርሃነመስቀል ገለጻ፤ ምክክሩ በአጭር ጊዜ ወደ ተግባር ቢገባ እየተስተዋሉ ያሉትን ቀውሶች መቀነስ ይቻላል፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች ከአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ የሚወርድላቸውን ኃላፊነት በአግባቡ በመወጣት ለምክክሩ ስኬታማነት የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ዶክተር ብርሃነመስቀል ዩኒቨርሲቲዎች ምክክር ኮሚሽኑ ችግር የሆኑበት ጉዳዮች ላይ በጥናትና በእውቀት የተደገፈ ሙያዊ እገዛ ማድረግ አለባቸው።በዚህ ረገድ ዩኒቨርሲቲያቸው የበኩሉን ድርሻ እንደሚወጣ ጠቁመዋል፡፡

# «ስአረንጓዴ ልማት ሽግግር...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ማሳደግ እንደሚገባ፤ ወደ አረንጓዴ ልማት ሽግግር ለማድረግ ለሚያስፈልገው የገንዘብ ድጋፍ ጠንካራ ዘዴ መፍጠር እና የዕዳ ቀውስን ማቆም ናቸው።

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ባወጣው መረጃ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከልዑክ ቡድናቸው ጋር በፈረንሳይ ፓሪስ በአዲስ የዓለም አቀፍ ፋይናንስ ስምምነት ጉባዔ ላይ መሳተፋቸው ታውቋል።

# ‹‹የዓባይ ግድብ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

የፖሊሲ ግብአቶችን እያፈራ ነው ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ይህም የወሰን ተሻጋሪ ወንዞች ፍትሐዊ አጠቃቀም ማስከበርና የዓባይን ተፋሰስ አገራትን አንድ ላይ ማምጣት ያስችላል ብለዋል፡፡

እንደ ም/ጠ/ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ግድቡ ትብብርንና የጋራ የውሃ ሀብት ፍትሐዊ አጠቃቀም ተምሳሌት ነው፡፡ የተቀናጀ ጥረት ማድረግና የዓባይን ተፋሰስ ልማት እምቅ አቅም በማንሳት የሕዝቦችን የመልማት ፍላጎት ማሳካት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

ግድቡ ለታችኛው የተፋሰሱ አገራት ትልቅ ጥቅም እንዳለው ኢትዮጵያ ታምናለች፤ ይሁንና ሊገጥሙ የሚችሉ ስጋቶችን ለመፍታት በአፍሪካ ኅብረት ለሚመራው የሦስትዮሽ ሂደት ቁርጠኛ መሆኗን ገልጸዋል፡፡ አንዳንድ አካላት የአፍሪካን ወንዝ የጋራ ተጠቃሚነትን በብቸኝነት ለመያዝ የሚያደርጉት ንግግር ኢትዮጵያን እንደማያደናቅፋትም አስገንዝበዋል፡፡

የውሃ ሀብት ፍትሐዊ አጠቃቀምን በተመለከተ የዓባይ ግድብ አንዱ ማሳያ መሆኑን የገለጹት አቶ ደመቀ፤ ግድቡ በአካባቢው የሚገኙ ሚሊዮኖችን ከድህነት ለማውጣት ያለመ አገራዊና አፍሪካዊ ፕሮጀክት ነው። ተመጣጣኝ የኤሌክትሪክ ኃይል በማቅረብ ግድቡ የቀጣናው ውህደት ዘዋሪ ይሆናል ብለዋል።

ኢትዮጵያውያን በግድቡ ያሳዩት ርብርብ አፍሪካውያን የአገር ውስጥ ሀብትን በማሰባሰብ ራሳቸውን ችለው ሜጋ ፕሮጀክቶች የመሥራት ብቃታቸውን የሚያሳይ መሆኑን ገልጸው፤ የዓባይ ግድብ አራተኛ ዙር ሙሌት ለመሙላት እየተቃረብን ነው ብለዋል፡፡

ከዚህ በፊት የተካሄዱት ሦስት ዙር ሙሌቶች የታችኛው ተፋሰስ ግዛቶች ላይ ተጽእኖ አላሳደሩም፡፡ ወደፊት የሚደረጉ ሙሌቶችም በተመሳሳይ ምንም ጉዳት አያደርሱም፡፡ የአፍሪካን የጋራ ወንዝ አጠቃቀም በብቸኝነት ለመቆጣጠር የሚጥሩ አንዳንድ ተዋናዮችን ንግግር በመቋቋም ፕሮጀክቱ በመጠናቀቅ ላይ ነውም ብለዋል።

እንደ አቶ ደመቀ ማብራሪያ፤ የዓባይ ወንዝ ተፋሰስ በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ ችግሮች እየተጐዳ ነው፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የሕዝብ ቁጥር መጨመርና ዘላቂነት የጎደለው አጠቃቀም የተቀናጀ የትብብር ጥረታችንን ከሚሹት የተፈጥሮ ተግዳሮቶች ጥቂቶቹ ናቸው። እንዲሁም የፖለቲካ ፍላጎት ማጣትና ከጋራ ሀብት ላይ ከፍተኛ ጥቅምን የማስጠበቅ ዝንባሌዎች ትብብርን እያደናቀፉ ናቸው፡፡

ተግዳሮቶች በአግባቡ ካልተፈቱ ቀጣይነት ያለው ልማትን የማረጋገጥ ምኞታችን ተቃራኒ ሆነው ይቀጥላሉ ያሉት አቶ ደመቀ፤ በተለይ ፍትሐዊና ምክንያታዊ የውሃ አጠቃቀምን ለማረጋገጥ ከዚህ ቀደም ያስመዘገብናቸውን ታላላቅ መርሆችን በማጎልበት የሚያጋጥሙንን ተግዳሮቶች ለመቋቋም ጥረታችንን የምናጠናክርበት ጊዜ አሁን ነው ብለዋል፡፡

የደቡብ ሱዳን የውጭ ጉዳይና ዓለም አቀፍ ትብብር ተጠባባቂ ሚኒስትር ዴንግ ዳው ዴንግ ማሌክ በበኩላቸው፤ ደቡብ ሱዳን በተፋሰሱ አገራት መካከል ያለውን ትብብር እንደምታምንና የድንበር ተሻጋሪ የውሃ ሀብቶችን ፍትሐዊና ምክንያታዊ በሆነ መልኩ መጠቀም ላይ እንደምታምን ተናግረዋል። ፍትሐዊ የውሃ ተጠቃሚነት ለሁሉም የተፋሰሱ አገሮች እንደሚጠቅምና ሊደግፉት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

ደቡብ ሱዳን የአየር ንብረት ለውጥንና የጋራ ድንበር ተሻጋሪ ሀብቶችን በጋራ ለመጠቀም እና ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔዎች የሚለውን መሪ ቃል ለመከተል ቁርጠኛ ነች ያሉት ኃላፊው፤ በኮንፈረንሱ ላይ የተገኙት የተፋሰሱ አገራት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮችና ተወካዮች ድንበር ተሻጋሪ የውሃ ሀብቶችን በፍትሐዊነት በመጠቀም ትብብርን ማሳደግ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአማራና የትግራይ ሕዝቦች አብሮነት በጠንካራ መሰረት ላይ የጸናና የማይነጣጠል ነው!

የአማራ እና የትግራይ ሕዝቦች ለዘመናት አብረው የኖሩ፤ ረጅም የጋራ ታሪክ የሚጋሩ፤ ተመሳሳይ ባህልና ኃይማኖት ያላቸው ናቸው።የትግራይ እና የአማራ ሕዝብ ትስስር ከጉርብትና ያለፈ በደምና በስጋ የተሳሰሩ፤ ተመሳሳይም ስነ ልቦናን የሚጋሩና ኢትዮጵያን አጽንተው ያቆዩ ወንድማማች ሕዝቦች ናቸው፡፡

የአማራና የትግራይ ሕዝቦች የአገሪቱ ሉአላዊነት ለመዳፈር የሚመጡ ባዕዳን ወረራዎችን በጋራ መክቶ በማስቀረትና የኢትዮጵያን ሉአላዊነት እንዳይደፈር የደምና የአጥንት መስዋዕትነት የከፈሉ ሕዝቦች ናቸው።በኢትዮጵያ የመንግስት አስተዳደር ስልጣንና ስልጣኔ አመጣጥ ሂደት ላይም ተመጋጋቢ፣ ተወራራሽ ፣ እንዲሁም ተዛማጅነት ያላቸው አካሔድ የነበራቸው ሕዝቦች ከመሆናቸውም ባሻገር ከሌሎች ወንድም ሕዝቦች ጋር በመሆን ለኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት መጠናከር የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ሲያበረክቱ የኖሩም ናቸው፡፡

ሁለቱ ሕዝቦች በተጎራባች አካባቢያዊ አቀማመጥ የሚኖሩ ከመሆናቸውም ባሻገር ኢትዮጵያዊ በመሆናቸውም ተመሳሳይ ባህል፤ ልማድና ወግ የሚጋሩም ናቸው።አብዛኛው ሕዝብም የሚተዳደረው በግብርና በመሆኑም ኢኮኖሚያዊ መሰረታቸውም ተመሳሳይ ነው፡፡

በተለያዩ የውሸት ትርክቶች እነዚህን ሕዝቦች ለማጋጨትና ለመለያየት በርካታ ሙከራዎች ተደርገዋል።በተለይም ለሁለት ዓመታት በቆየው ጦርነት ምክንያት ሁለቱ ሕዝቦችም እጅግ ውድ የሚባል ዋጋ ለመክፈል ተገድደዋል።በጦርነቱ ምክንያትም በሁለቱም ወገኖች በርካታ ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመት ተከስቷል።ይህ ደግሞ ከሁለቱ ሕዝቦች አልፎ እንደ አገር ያስከፈለው ዋጋ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡

ሆኖም መንግስት ባደረገው ከፍተኛ ጥረት ለሁለት ዓመታት የተካሄደው ጦርነት በፕሪቶርያ በተደረገው ስምምነት አማካኝት ተቋጭቶ በምትኩ ሰላም ሰፍኗል።ይህንኑም ተከትሎ በአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ የተመራ የልዑካን ቡድን በመቀሌ በመገኘት ጉብኝት አካሂዷል።በተመሳሳይም በትግራይ ክልል ጊዚያዊ አስተዳደር ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጌታቸው ረዳ የተመራ ልዑክ በባህርዳር ከተማ በመገኘት የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱን ማጠናከር የሚያስችል ውይይት አድርጓል፡፡

ይህ በጎ ጅምር ነው።የሁለቱ ርዕሰ መስተዳድሮች ጉብኝት ለጊዜው ሻክሮ የቆየውን ግንኙነት የሚያድስና ፍጹም ሰላማዊ ወደ ሆነ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትም እንዲያድግ በር የሚከፍት ነው።ከፕሪቶርያው ስምምነት በኋላም እንደአገር የሰፈነው ሰላምም የሁለቱን ክልል ሕዝቦች የበለጠ የሚያቀራርብና ዘመናት የተሻገረውን አብሮነት የሚያድስ ነው።የአማራና የትግራይ ሕዝቦች ዘርፈ ብዙ መስተጋብሮች ያሉትና ለዘመናት ተሳስሮ የኖረና ወደፊትም አብሮ የመኖር እጣ ፈንታ ያለው በመሆኑ የሁለቱ መስተዳድሮች ጉብኝት ወዳጅነቱ ዘላቂ መሰረት እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የአማራም ሆነ የትግራይ ሕዝቦች የጦርነት አስከፊነት በሚገባ የሚገነዘቡ ሕዝቦች ናቸው። በታሪክ በተደጋጋሚ ጦርነት ባስተናገደው የሰሜኑ ክፍል ሁለቱም ሕዝቦች የሚኖሩ እንደመሆኑ ከጦርነት የሚገኝ አንዳች ትርፍ እንደሌለ ለሁለቱም ሕዝቦች ነጋሪ አያስፈልጋቸውም።ከጦርነት ሞት፤ አካል መጉደል፤ መፈናቀልና ስደት እንዲሁም መታረዝ እንጂ የሚገኝ ጥቅም እንደሌለ ሁለቱም ሕዝቦች በውል ያውቁታል፡፡

ሁለቱን ሕዝቦች ወደ ግጭት ሊያስገባ የሚችል አንዳችም ምክንያት አይኖርም።የሚነሱ ጥያቄዎች ሲኖሩም የአገሪቱን ህጎች ተከትለው የሚፈቱ በመሆናቸው በሁለቱም ክልል የሚገኙ አመራሮች በሳልና አንድነትን ለሚያጸና ተግባር ራሳቸውን ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከዚህ ባሻገር ግን ሁለቱ ሕዝቦች የሚያስፈልጋቸው የቆየውን የርስ በዕርስ ግንኙት ማጠናከር፤ የንግድ ልውውጥን ማጠናከር፤ ከፋፋዮችን ለመመከት በጋራ መቆም ብቻ ነው፡፡

የተፈጠሩም ሆነ ወደፊት ለሚፈጠሩ ችግሮች በምንም አይነት መልኩ ከትግራይና አማራ ሕዝቦች አቅም በላይ አይደሉም። በአጠቃላይ የትግራይ እና የአማራ ሕዝቦች በጋራና በሰላም መኖር ለኢትዮጵያ ቀጣይ አንድነትና ህልውና የሚኖረው ፋይዳ የላቀ በመሆኑ የሁለቱ ሕዝቦች ግንኙነት እስከ አሁን ከነበረው በበለጠ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል!


**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የገቢ አሰባሰብ ሂደቱ አገራዊ የሃብት ፍላጎቱን ያገናዘበ ይሁን

ማሙሻ ከአቡርሻ

ግብር/ታክስ፣ በአንድ ሀገር የተረጋጋ መንግስታዊ ስርዓት እንዲኖር፣ ዜጎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግባሮቻቸውን በሰላማዊ መንገድ እንዲያከናውኑ እና ከመንግስት ማግኘት የሚፈልጓቸውን አገልግሎቶች ማግኘት እንዲችሉ የመንግስት ዋነኛው አቅምና መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግል ነው። በመሆኑም መንግስት መንግስታዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት፤ ለዜጎችም ሰላምና ደህንነት መረጋገጥ፤ ልማትና የመሰረታዊ ፍላጎቶቻቸው ጥያቄዎች መመለስ፣ መንግስት ግብር የመሰብሰብ ሥልጣን፤ ዜጎችም ግብር የመክፈል ግዴታ አለባቸው።

ምክንያቱም ግብር መክፈል መንግስት ለሕዝቦች ጥያቄ መልስ መስጠት የሚያስችለውን የልማትና ተያያዥ ተግባራትን ለመከወን ብቻ ሳይሆን፤ ከዚህም ከፍ ያለ አገራዊ ክብር (የደህንነት እና ሉዓላዊነት ጥያቄን የመመለስ) አስጠብቆ የመዝለቅ አለመዝለቅን ሁኔታ የሚመለከት ነው። በመሆኑም ግብር/ታክስ መክፈል የአንድ አገር ዜጎች በቅድመ ሁኔታ ያልታጠረ ግዴታ ሲሆን፤ ይሄን ግዴታን መወጣት ደግሞ ከፍ ያለ የስልጣኔ፣ የአገርና ሕዝብ ወዳድነት መገለጫ ባህሪ ነው።

### የግብር/ታክስ ዓላማዎች

የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚያስረዱት፣ በአንድ አገር ውስጥ መንግስት በዋነኛነት በሁለት መንገድ ገቢን ይሰበስባል። አንዱ በግብር እና በታክስ አማካኝነት፤ ሁለተኛው በእቃ እና አገልግሎት ክፍያ አማካኝነት። እነዚህ ገቢዎችም የየራሳቸው ዓላማ ኖሯቸው የሚሰበሰቡ ናቸው።

ለምሳሌ፣ በግብር አማካኝነት የሚሰበሰበው ገቢ ሕዝቦች ተጠቃሚ የሚሆኑባቸው የመሰረተ ልማት አቅርቦቶች ወጪ መሸፈኛ የሚውል ነው። በዚህም እንደ መንገድ፣ ውሃና መብራት የመሳሰሉ ማንኛውም ዜጋ በወል የሚጠቀምባቸው መሰረተ ልማቶችን ለዜጎች (ታክስ ከፈለም አልከፈለም) ተደራሽ የሚደረግበት ነው።

በአንጻሩ ከእቃ እና አገልግሎት ክፍያ የሚሰበሰበው ገንዘብ፣ የእቃው ወይም የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እና የሚጠቀመውም መጠን ተለይቶ የሚታወቅበት ነው። በመሆኑም በዚህ መልኩ ከግብር እና ታክስ እንዲሁም ከእቃ እና አገልግሎት የሚሰበሰበው ገቢ ዋነኛ ዓላማ መንግስት ለስራ የሚያስፈልገውን ገቢ እንዲያገኝ ማስቻል ነው።

ሁለተኛው የግብር ዓላማ፣ ኢኮኖሚን ወይም ካፒታልን የመምራት ሲሆን፤ የንግዱ ማህበረሰብ ተቀዳሚ ዓላማው ትርፍ ማግኘት እንደመሆኑ የተሻለ ትርፍ በሚያስገኝለት የስራ መስክ ላይ መሰማራት ይፈልጋል። መንግስት ደግሞ የሕዝቦችን ኑሮ ለማሻሻል እና ለህዝቡ የመሰረተ ልማት አቅርቦቱን በተገቢው ሁኔታ እንዲዳረስ ለማድረግ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ዘርፎች ይኖራሉ። በመሆኑም ባለሃብቱ በእነዚህ መስኮች ቢሰማራ ውጤታማ የሚሆንበትን አነስተኛ ግብር ማስከፈልን የመሳሰሉ ርምጃዎችን ይወስዳል። በመሆኑም በዚህ መልኩ የሚሰበሰብ ግብር እና ታክስ የሃብት ስምሪቱን/ኢኮኖሚውን የመምራት አቅም ይፈጥርለታል።

በሌላ በኩል፣ መንግስት ታክስና ግብርን የሕዝቡን ጤና እና የሕዝቡን ማህበራዊ ኑሮ ለመጠበቅ ይጠቀምበታል። ለምሳሌ፣ ሲጋራ፣ የአልኮል መጠጦች እና ሌሎችም ምርቶች የሕዝቡን ጤና ይጎዳሉ፤ የሕዝቡን ማህበራዊ ኑሮ ያናጋሉ፤ ቤተሰብን ይበትናሉ። ስለዚህ ሕብረተሰቡ እነኚህን ምርቶች እንዳይጠቀም ዋጋቸው ከፍ እንዲል በማድረግ ገቢውንም ያሳድጋል፤ የሕብረተሰቡንም ጤና ለመጠበቅ ያስችለዋል።

ከእነዚህ ዓላማዎች በተጓዳኝ፣ ግብር እና ታክስ መንግስት የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪን እንዲያስፋፋ የሚያግዙት ሲሆን፤ በተለይ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ እቃዎች ላይ ከፍተኛ ቀረጥ በመጣል እንዲሁም ለአገር ውስጥ አምራቾች ማበረታቻ በማድረግ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማገዝ አቅም ይፈጥርለታል።

በዜጎች መካከል ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል (ዌልዝ ዲስትሪቡሽን) እንዲኖር ለማድረግም ታክስ ጉልህ ሚና ያለው ሲሆን፤ በዚህም መንግስት ትልቅ ገቢ ያላቸው እና ቅንጡ ኑሮን የሚኖሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ከፍ ያለ ታክስ ከፍለው ድሃው ሕዝብ የሚደጎምበትን እድል ለመፍጠር ያስችለዋል።

በኢትዮጵያም እነዚህን ዓላማዎች ማዕከል ያደረጉ የግብር እና ታክስ አሰራር ስርዓቶች ተዘርግተው ዘርፈ ብዙ ተግባራት እየተከናወኑ ሲሆን፤ ለእነዚህ አሰራሮች የሚሆኑ የሕግ ማዕቀፎች ተቀርጸው እና አደረጃጀቶችም ተፈጥረው ነው እየተሰራ ያለው። ለምሳሌ፣ ገቢዎች ሚኒስቴር አጠቃላይ ከገቢ እና ግብር ጋር ያሉ ጉዳዮችን ይዞ የሚሰራ ተቋም ሲሆን፤ ጉሙሩክ ኮሚሽንም የገቢና ወጪ ምርቶችን የማሳለጥ፣ የቀረጥና መሰል ጉዳዮችን የሚከውን ነው። ለዚህም የሚሆን አደረጃጀት፣ በጀትና የሕግ ማዕቀፎች ተዘጋጅተው ነው እየተከናወነ ያለው።

### ግብር እና ታክስ በኢትዮጵያ

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ በኢትዮጵያ የግብር እና ታክስ ስርዓት ከአክሱም ዘመን ጀምሮ ሲተገበር የቆየ ሲሆን፤ በዘመን ጅረት ውስጥ የተለዋወጡ መንግስታትም ይሄንኑ የግብር እና የታክስ ሂደትን የመንግስት አቅም አድርገው ተጠቅመውበታል። አገርና ሕዝብንም በሁሉም መስክ መርተው ማሻገር ችለዋል።

ቀደም ሲል እንዳነሳሁት ደግሞ ከግብር እና ታክስ መሰረታዊ ዓላማዎች አንዱና ቀዳሚው የመንግስትን ዓመታዊ የገንዘብ/ሃብት ፍላጎት የሚያሟላ ገቢ መሰብሰብ ነው። ከዚህ አኳያ ተልዕኮ ተሰጥቶት ግብር እና ታክስን እየሰበሰበ ያለው የገቢዎች ሚኒስቴር ሲሆን፤ በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮችም ለዚሁ ፍላጎቶቻቸው ማሳኪያ የሚሆን ሃብት የሚያሰባስቡ ቢሮዎች ተደራጅተዋል። በዚህ ረገድ በተለይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እያደገ የመጣውን የመንግስትን የበጀት ፍላጎት ተከትሎ ተቋማቱ ይሄንን ፍላጎት ባማከለ መልኩ ግብርን የመሰብሰብ ከፍ ያለ ኃላፊነት ወስደው እየሰሩ ይገኛል።

ይሁን እንጂ ካለው አቅም አንጻር በሚፈለገው ልክ ሃብት መሰብሰብ እንዳልተቻለ ግን የዘርፉ ምሑራን ይገልጻሉ። ለዚህ እንደማሳያ የሚያቀርቡትም፣ የአገር ውስጥ አጠቃላይ ምርት (ጂ.ዲ.ፒ) እና የሚሰበሰበው ታክስ መካከል ያለው ግንኙነት ባለፉት ዓመታት እየቀነሰ መምጣቱን ነው። ይሄ ደግሞ በአንድ በኩል፣ ህብረተሰቡ የግብር ግዴታውን በተገቢው መንገድ እየተወጣ አለመሆኑን፤ በሌላ በኩል መንግስት ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሃብት ተገቢውን ድርሻ እያገኘ አለመሆኑን አመላካች ስለመሆኑ ነው የሚያስረዱት።

ይሄ ደግሞ ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሃብት ለመንግስት መሰብሰብ የሚገባውን ገቢ በመሰብሰብ ረገድ ትልቅ ክፍተት መኖሩን አመላካች ነው። ይሄ ደግሞ እንደ ተቋምም እንደ አገርም የሚታይ ድክመት ሲሆን፤ ይሄንን ለማሻሻል በየጊዜው የተወሰዱ ርምጃዎች እና የተገኙ ውጤቶች ቢኖሩም አሁንም ድረስ በጅምር ደረጃ የሚወሰዱ እንጂ አጥጋቢ የሆነ ውጤት ተገኝቷል ለማለት አያስችልም።

ይሄንን ለመረዳት አገራዊ የበጀት እድገቱን፣ የገቢ ፍላጎቱን፣ ከአገር ውስጥ ገቢ የሚጠበቀውን ሃብት፣ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚይዘውን ዓመታዊ የገቢ ስብሰባ እቅድ እንዲሁም አፈጻጸሙን መመልከቱ ተገቢነት ይኖረዋል። ለምሳሌ፣ የገቢዎች ሚኒስቴር በ2014 በጀት ዓመት 360 ቢሊዮን ብር ሊሰበስብ እቅድ ይዞ፤ ከዚህ ውስጥ 336 ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር በመሰብሰብ የእቅዱን 93 ነጥብ 53 በመቶ ነው ማሳካት የቻለው። በተመሳሳይ መልኩ በ2015 ዓ.ም 450 ቢሊዮን ብር (266 ነጥብ 95 ቢሊዮን ብር ከአገር ውስጥ ታክስ እንዲሁም 183 ነጥብ 34 ቢሊዮን ብር ከወጪ ንግድ፣ ቀረጥና ታክስ) ለመሰብሰብ ነው እቅድ የያዘው።

ወደ 6ኛው ገጽ ዞሯል

# ነፃ ሃሳብ

## የገቢ አሰባሰብ ሂደቱ...

ከገጽ 5 የዞረ

ይሄንን እቅዱን ማሳካት አለማሳካቱ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ የሚታወቅ ቢሆንም፤ ሚኒስቴር መስሪያቤቱን የሚከታተለው ቋሚ ኮሚቴ አባላት ግን፤ በአሥር ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ መሠረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በ2015 ዓ.ም ማቀድ የነበረበት አጠቃላይ ገቢ 497 ቢሊዮን ብር ሊሆን ይገባው እንደነበር መግለጻቸው የሚታወቅ ነው።

ይሄም የሚያሳየው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ምንም እንኳን በእቅድ አፈጻጸም ረገድ ውጤታማ ነኝ ቢልም፤ በአንድ በኩል ሊያሳካ ያቀደውን እንኳን ሙሉ በሙሉ አለማሳካቱን፤ በሌላ በኩል አገራዊ የገቢ ፍላጎቱንና መሪ እቅዱን ማዕከል አድርጎ አለማቀዱን (በቋሚ ኮሚቴው አቅጣጫ መሰረት የ2015 ብቻ የ47 ቢሊዮን ብር ልዩነት ማሳየቱን ልብ ይሏል) ነው መረዳት የሚቻለው።

### የታክስ ሥርዓቱ ፈተናዎች እና መፍትሄዎች

በኢትዮጵያ የታክስ እና ግብር ሥርዓቱን ውጤታማ ለማድረግ በአደረጃጀትም፣ በሕግ ማዕቀፍም የተለያዩ ማሻሻያዎች እየተወሰዱ፣ መጠነኛ ለውጥም እየታየ ቢሆንም፤ ዛሬም ድረስ የግብር አስተዳደር ሥርዓቱን እየፈተኑ የዘለቁ በርካታ ችግሮች አሉ። በዚህ ረገድ ተቋማዊ ጉዳዮች፣ የሕግና አሰራር፣ የግብር ከፋዩ አመለካከትና የሞራል ደረጃ፣ የሕብረተሰቡ የባለቤትነት መንፈስ እንዲሁም ከሰላምና ፀጥታ ጋር ተያይዘው የሚነሱ አንኳር ጉዳዮች ተጠቃሽ ናቸው።

ለምሳሌ፣ ከተቋም እንዲሁም ከሕግ እና አሰራር ጋር በተያያዘ የሚነሱ ችግሮች አሉ። እነዚህ አንድም በተቋማት ያለው የሰው ኃይል በእውቀት፣ ክህሎት እና ሥነምግባር ጋር የሚያያዝ ሲሆን፤ በዚህም ግብር ሰብሳቢውም ሆነ አጋር አካላት የታቀደውን ገቢ እንዲሰበሰብ ከማድረግ አኳያ ከሰው ኃይላቸው አሰራር አንጻር በሚገለጽ ችግር ሲያጋጥማቸው ይታያል። ይሄም አሰራሩን በውል ተገንዝቦ ካለመተግበር ጀምሮ ይሁነኝ ተብሎ ከአሰራሩ ባፈነገጠ መንገድ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ለብልሹ አሰራርና ላልተገባ ጥቅም ማካበቻ የሚያደርጉበት ሂደት ነው።

በሌላ በኩል የሚነሳው የግብር ከፋዩ የሕግ ተገዢነት እና የሞራል ሁኔታ ሲሆን፤ በዚህም በአንድ በኩል ግብር ከፋዩ አካል ለሕግ እና ለሞራል እሴቶች ተገዢ ከመሆን ይልቅ፣ በግብር ስወራና ማጭበርበር ላይ ተሰማርቶ መገኘቱ፤ በሌላ በኩል፣ የሕግ ክፍተቶችን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም መክፈል የሚገባውን ታክስና ግብር ላለመክፈል ሲተጋ መታየቱ ነው።

በሕብረተሰቡ ውስጥ ያለው የያገባኛል ስሜት አናሳ መሆን እና ከሕግ ማስከበር ርምጃዎች ደካማነት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮችም ተደማሪ የታክስ ሥርዓቱ ፈተናዎች ናቸው። ለዚህም አንድም ሕብረተሰቡ የግብር ጉዳይ የሰላሜ፣ የልማቴ፣ የሉዓላዊነትና ብልጽግናዬ መሰረት ነው ብሎ ያለማሰብ፤ ሁለተኛም፣ የሚሰበሰበው ግብር ለሚፈለገው ዓላማ አይውልም ብሎ እምነት የማጣት ጉዳይ ይነሳል።

ይሄ ደግሞ በአንድ በኩል ግንዛቤ ያለመፍጠር ክፍተት የወለደው ሲሆን፤ በሌላ በኩል ግን ሕብረተሰቡን እምነት እንዳይኖረው የሚያደርጉ የሕግ ጥሰቶች ሲፈጠሩ አስተማሪ እና ሕዝቡ “አጥፊዎች እንዲህ ከተቀጡ እኔም ግብር ሰዋሪዎችን የማጋለጥ ኃላፊነቴን ልወጣ” የሚል መንፈስን እንዳይሰንቅ የሚያደርገው ነው። በመሆኑም የግንዛቤ ክፍተት እና የሕግ ማስከበር አሰራሩ መላላት ህብረተሰቡ የዚህ ተግባር ንቁ ተዋናይ እንዳይሆን አድርጎታል ማለት ይቻላል።

ሌላው፣ ኮንትሮባንድ እና ሕገወጥ ንግድ ነው። ኮንትሮባንድን በመከላከል ረገድ በተለይም በጉሙሩክ ኮሚሽን እና ባለድርሻ ተቋማት በኩል ዘርፈ ብዙ ተግባራት እየተከናወኑ ናቸው። በዚህም አበረታች የሚባል ውጤት እየተገኘ ቢሆንም፤ ችግሩን በሚፈለገው ደረጃ መቅረፍ ባለመቻሉ ጠንካራ እና አስተማሪ ርምጃዎችን በመውሰድ የታገዘ ስራን መከወን ይጠይቃል።

> **አገራዊ የገቢ ፍላጎቱንና መሪ እቅዱን ማዕከል አድርጎ አለማቀዱን (በቋሚ ኮሚቴው አቅጣጫ መሰረት የ2015 ብቻ የ47 ቢሊዮን ብር ልዩነት ማሳየቱን ልብ ይሏል)**

ምክንያቱም፣ ዛሬ ላይ ኮንትሮባንድ እና ሕገወጥ ንግድ፣ ገቢን መሰወር፣ የሕግ ተገዢነት ማነስ፣ የግብር መክፈል ሞራላዊ ልምሻ፣ የአሰራርና ቴክኖሎጂ ውስንነቶችን የመሳሰሉ ችግሮች የገቢ አሰባሰብ ሥርዓቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሲያሳድሩ ተስተውሏል። ከዚህ በተጓዳኝ ከሰላምና ጸጥታ ጋር በተያያዘ በየጊዜው የሚስተዋሉ ችግሮች በርካታ ግብር ከፋዮች ከግብር ሥርዓቱ ውጪ ሆነው እንዲቆዩ በማድረግ የገቢ አሰባሰብ ሂደቱ ላይ ጥላ ማጥላታቸው አልቀረም።

በመሆኑም ችግሩን ከመቅረፍ እና ገቢን ከማሳደግ አኳያ የሰው ኃይሉን፣ ተቋማዊ አደረጃጀትን እና የቴክኖሎጂ አቅምን ማጎልበት፤ የሰላምና ጸጥታ ጉዳዮችን ሰላማዊ እልባት መስጠት፤ የሕብረተሰቡን የባለቤትነት መንፈስ በማሳደግ እና ተሳታፊ ማድረግ፤ የሕግ ተገዢነትን እና ተጠያቂነትን ማስፈን የመሳሰሉ ርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊም፣ ተገቢና የግድም ነው።

በተለይ የታክስ እና ግብር አሰባሰብ ሂደቱን ውጤታማ ከማድረግ (የኮንትሮባንድ እና ሕገ ወጥ ንግድ፣ የገቢ መሰወር፣ የደረሰኝ አለመቁረጥ እና ተየያዥ ችግሮችን ከማቃለል) አኳያ በቴክኖሎጂ መታገዝ ካልተቻለ፤ የታክስ አስተዳደሩ የሚፈለገውን አይነት ውጤት ሊያመጣ አይችልም። ምክንያቱም ቴክኖሎጂው ሥራን በጥራትና በቅልጥፍና ከመከወን ባሻገር ከአሰራር ብልሹነት ጋር የሚፈጠሩ ችግሮችን ፈር ለማስያዝ ያስችላል።

ከዚህ ጎን ለጎን የሕብረተሰቡን የታክስ ንቃተ ሕሊና ማሳደግ ይገባል። ይህ ሲሆን በአንድ በኩል ግብር ለምን እና ለማን እንደሚከፍል፣ የሚከፍለው ግብር ለምን ዓላማ እንደሚውል እንዲገነዘብና ግብርን በኃላፊነት እንዲከፍል ያስችለዋል። በሌላ በኩል የንግዱ ማህበረሰብ ዘንድ ከደረሰኝ አለመስጠት ጋር ለተያያዘው ችግር መፈታት አጋዥ አቅም እንዲሆን ያስችላል። ከዚህ በተጓዳኝ ከታክስ ፖሊሲው ጋር የተያያዙ ችግሮችን የማሻሻል፤ በታክስ አስተዳደሩም ላይ ያሉ ችግሮችን የማስወገድ ርምጃዎችን መውሰድ ይገባል።

### የመንግስት የበጀት ወጪና ገቢ ፍላጎቶች ምልከታ

ወደ ጉዳዩ ለመዝለቅ ያመቸን ዘንድ ቀደም ያሉትን ሦስት እና አራት ዓመታት የመንግስትን የበጀትና የገቢ ሁኔታ ለመዳሰስ ልሞክር። ለምሳሌ፣ ከ2011 እስከ 2013 በጀት ዓመት ጠቅላላ የመንግስት ገቢ 18 ነጥብ 6 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት ያስመዘገበ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ የታክስ ገቢ ዓመታዊ ዕድገት 18 ነጥብ 3 በመቶ እንደነበር ነው የገንዘብ ሚኒስቴር መጋቢት/2014 ዓ.ም ያወጣው የመካከለኛ ዘመን /2015-2019/ የማይክሮ ኢኮኖሚ እና ፊሲካል ማዕቀፍ ሰነድ ያመለክታል።

በዚህ ሰነድም ሆነ የኢፌዴሪ የ2015 በጀት ዓመት የተደገፈ በጀት ሰነድ ላይ እንደተመላከተው፤ በእነዚህ ሦስት ዓመታት የታክስ ገቢ በአማካይ 79 ነጥብ 3 በመቶ በመሆን ከአጠቃላይ የመንግስት ገቢ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘ ቢሆንም፤ ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ግን በ2010 ከነበረበት 10 ነጥብ 7 በመቶ በማሽቆልቆል በ2013 ዘጠኝ በመቶ ሆኗል።

ይሄንን ለማሻሻል በታክስ ፖሊሲና በታክስ አስተዳደር ላይ የተደረጉ በርካታ ማሻሻያዎች ኢኮኖሚው ከገጠመው ተግዳሮት ጋር ተያይዞ ውጤት ሊያሳዩ እንዳልቻሉም ነው መረጃዎቹ የሚያመለክቱት። የውጪ እርዳታም ቢሆን ቅናሽ የታየበት ነበር።

በሌላ በኩል፣ በእነዚህ ሦስት ዓመታት ጠቅላላ የመንግስት ወጪ በየዓመቱ የ19 በመቶ ዕድገት ያሳየ ሲሆን፤ የመደበኛ ወጪ የ20 በመቶ እና የካፒታል ወጪዎች የ18 በመቶ ዓመታዊ አማካይ ዕድገት አስመዝግበዋል።

የ2014 በጀት ዓመትን በተመለከተም፤ የፌዴራል መንግስት ወጪ ለመሸፈን 436 ቢሊዮን ብር ከታክስና ታክስ ካልሆኑ ገቢ እና ከውጭ ዕርዳታ ለማግኘት፤ 106 ቢሊዮን ብር የሚሆነውን የበጀት ጉድለት ደግሞ 38 ቢሊዮን የውጭ እና 68 ቢሊዮን የአገር ውስጥ የተጣራ ብድር በመውሰድ መሸፈንን ታላሚ ያደረገ ነበር። በሰሜኑ ኢትዮጵያ የተከሰተው ጦርነት ያደረሰው ከፍተኛ የሰብዓዊና የኢኮኖሚ ጉዳት በመንግስት ላይ ተጨማሪ የወጪ ፍላጎት መጠየቁ ይታወቃል።

786 ነጥብ 61 ቢሊዮን ብር የተያዘለት የ2015ም ከታክስ ገቢ፣ ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች እና የውጭ ዕርዳታ የገቢ ምንጮችን በመተማመን የተዘጋጀ ሲሆን፤ በእቅድ የተቀመጠው የ477 ነጥብ 78 ቢሊዮን ብር ገቢ እና የ786 ነጥብ 61 የመንግስት ወጪ መካከል የ308 ነጥብ 83 ቢሊዮን ብር (የአገር ውስጥ ምርት 3 ነጥብ 4 በመቶ ድርሻ ያለው ነው) የበጀት ጉድለት መኖሩን ነው የኢፌዴሪ የ2015 በጀት ዓመት የተደገፈ በጀት ሰነድ ላይ የተመላከተው።

ግንቦት 2015 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት 21ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ቀርቦ 801 ነጥብ 65 ቢሊዮን ብር እንዲሆን ውሳኔ ያገኘው እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ለዝርዝር እይታ ወደ ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶ ያለው የ2016 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት ረቂቅ በጀት፤ በጀቱ የፌዴራሉን መንግሥት በአስር ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ ያስቀመጣቸውን ታላሚ ግቦች ታሳቢ ያደረገ ስለመሆኑ ነው የተነገረው።

በዚህም ለፌደራል መንግሥት መደበኛ ወጪዎች 369 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር፣ ለካፒታል ወጪዎች 203 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር፣ ለክልሎች የሚሰጥ ድጋፍ 214 ነጥብ 07 ቢሊዮን ብር፣ ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ድጋፍ 14 ቢሊዮን ብር እንዲውል የታሰበ ነው።

በጀቱ ከዓምናው በጀት አንጻር መጠነኛ ጭማሪ ያለው ቢሆንም፤ እንደ 2015ቱ ሁሉ ከፍ ያለ የበጀት ጉድለት የታየበት ስለመሆኑም ነው የተመላከተው። በዚህም የ281 ቢሊዮን ብር ጉድለት የታየበት ሲሆን፤ ይሄ ደግሞ መንግስት የበጀት ጉድለቱን ለመሙላት ከአገር ውስጥ እና ከውጪ ብድር ለመውሰድ እንደሚገደድ አመላካች ነው።

ረቂቅ በጀቱ ለምክር ቤት በቀረበበት ወቅት ወጪውን ለመሸፈን ይችል ዘንድ ከአገር ውስጥ ገቢ እና ከውጪ አገር ርዳታ ምንጮች 520 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ያቀደ ሲሆን፤ የበጀት ጉድለቱ 242 ቢሊዮን ብር ከአገር ውስጥ ብድር፣ ቀሪው 39 ቢሊዮን ብር ከውጭ ብድር እንደሚሸፈን መገለጹም ይሄንኑ የሚያረጋግጥ ነው።

በዚህ መልኩ የሚገለጸው አገራዊ የበጀት ወጪ እና የገቢ ሁኔታ የሚያስረዳው፤ ከግብር እና ታክስ የሚሰበሰበው ገንዘብ ከጊዜ ወደ ጊዜ የቁጥር መሻሻል ያሳያ ቢሆንም፤ ከመንግስት የወጪ እድገት እና የገቢ ፍላጎት አንጻር ሲታይ የሚፈለገውን ያህል አለመሆኑን ነው። ከዚህም በላይ ከአገር ውስጥ ምርት ጥምርታ አኳያ ሲታይ እያሽቆለቆለ ያለ እና ይሄንን ለማሻሻል ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንደሚገባ ያረጋገጠ እውነት መሆኑን ለመረዳት ያስችላል።

### እንደ መውጫ

በ2016 በጀት ዓመት ሊኖር የሚችለው የሃብት ፍላጎት እንዲሁም የታየው የበጀት ጉድለት መንግስት ለሚያከናውናቸው ተግባራት ከፍ ያለ ገቢ እንደሚፈልግ አመላካቾች ናቸው። በተለይ መንግስት የፋይናንስ ፍላጎቱን ለማሟላት ሲል ወደ ብድር አልያም ወደ ገንዘብ ሕትመት የሚገባ ከሆነ እንደ አገር ሊፈጥር የሚችለውን የዋጋ ንረት እና የኑሮ ውድነት ሁሉም ሊገነዘበው የሚችለው ሃቅ ነው። በመሆኑም ይሄ እንዳይሆን የአገር ውስጥ ገቢን ማሳደግ የቅድሚያ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ታላቅ የቤት ስራ ነው።

ይሄን የአገር ውስጥ ገቢ ማሳደግ እና ውጤታማ የግብር ስርዓት እውን እንዲሆን ደግሞ የአንድ ተቋም ወይም አካል ተግባር ብቻ ሊሆን አይገባም። ምክንያቱም ግብር ሰብሳቢው ተቋም እሰበስባለሁ ብሎ ስለተነሳ ብቻ የሚፈልገውን ሃብት/ገቢ መሰብሰብ አይችልም። በመሆኑም ግብር ሰብሳቢው ተቋም እና አጋር የመንግስት ኃይሎች (በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ)፤ ግብር ከፋዩ ማህበረሰብ እንዲሁም ሁሉም ዜጋ፤ በበጀት ዓመቱ ሊሰበሰብ የሚገባው ግብር ለእሱም ሆነ ለአገሩ ምን ማለት እንደሆነ ተገንዝቦ የበኩሉን ሚና ሊወጣ ይገባል።

እያሽቆለቆለ የመጣው የግብር እና የአገር ውስጥ አጠቃላይ ምርት (ጂ.ዲ.ፒ) ጥምርታ ገጽታም መቀየር ያስፈልጋል። ምክንያቱም ሁነቱ ህብረተሰቡ የግብር ግዴታውን እየተወጣ፤ መንግስትም ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሃብት ገቢ እየሰበሰበ እንዳልሆነ እማኝ ነው። ይህ ደግሞ መንግስት ለሕዝቡ ማድረስ የሚገባውን አገልግሎት እንዳያዳርስ፤ የመሰረተ ልማት ስራዎቹም እንዲቀንሱ ያስገድደዋል።

በመሆኑም የግብር አሰባሰብ ሂደቱን ውጤታማ ለማድረግ መስራት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ መንግስት (እንደ አጠቃላይ ተቋማት እና መዋቅሩ) የተያዘውን በጀት እና የሚሰበሰበውን ሃብት በአግባቡ (በቁጠባ እና ለታለመለት ዓላማ ብቻ እንዲውል በማድረግ) መጠቀም ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም ሃብቱም የሚፈለገውን ውጤት የሚያመጣው ለታለመለት ዓላማ ሲውል፤ ሕብረተሰቡም ለመክፈልም፣ እንዲከፈል ድርሻ ወስዶ ለመስራትም ተነሳሽነትና ቁርጠኝነቱ የሚኖረው የተሰበሰበው ግብር የሚታይ ስራ ተሰርቶበት ሲመለከትና ከልማቱም ተጠቃሚነቱን ሲያረጋግጥ ስለሆነ ነው።

በመሆኑም መንግስትም፣ ህብረተሰቡም የየድርሻውን ከተወጣ ታክሱ ተሰብስቦ የአገራችንን ልማት ወደፊት ማራመድ ይችላል። ለዚህ ደግሞ ሁሉም ዜጋ “ይሄንን የማደርገው ለማንም ብዬ ሳይሆን፤ ለራሴ፣ ለልጆቼ፣ ለወገኖቼ፣ ለአገሬና እንደ አጠቃላይ ለሕዝቤ ነው” የሚል መንፈስን ሊላበስ ይገባል። መንግስትም በጀቱንም አሰራሩንም ግልጽ ማድረግ አለበት።

በመሆኑም የ2016 በጀት ዓመት የገቢ አሰባሰብ ሂደቱ አገራዊ የሃብት ፍላጎቱንና የበጀት ጉድለቱን ያገናዘበ ሊሆን ይገባዋል። “በ2022 ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ተገንብቶ አገራዊ ወጪ በታክስ ገቢ ተሸፍኖ ማየት” የሚለው የገቢዎች ሚኒስቴር ርዕይ ሊሳካ የሚችለውም፤ ቃልን በጽሑፍ ከማኖር ያለፈ ዘመናዊ የታክስ አሰባሰብ ሥርዓትን እውን በማድረግ እና ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን የታክስ ገቢ በመሰብሰብ ሲገለጽ ነው። ይህ ሲሆን ነው አገራዊ የወጪ ፍላጎቱ በራሱ አቅም ሊፈጽም የሚችለው።

# የኮንሶ ድምቀቶች

**ዳግም ከበደ**

ኢትዮጵያውያን ውብ ድብልቅ ማንነት ያላቸው ሕዝቦች የሚኖሩባት ምድር ነች። እነዚህን ሕዝቦች ከቀሪው ዓለም የሚለያቸው በርካታ ባሕላዊ እሴቶች መያዛቸው፤ ከራስ ማንነት የሚቀዱ ብዝኃ እሴቶች ማካተታቸው ጭምር ነው። የኢትዮጵያን ምድር የረገጠና አስተውሎ ለመረዳት የሞከረ ሁሉ በሕዝቦች ኅብረት፣ አመጋገብ፣ አብሮ የመኖርና የመቻቻል፣ የቋንቋ፣ የአለባበስና የተለያዩ የኃዘን፣ የደስታ ሥርዓቶቻችን ሳይደመም አያልፍም። ከሁሉ በላይ ግን እጅግ ማራኪና በሌላ አገር የማያገኛቸው አስደናቂ እሴቶች እንደሆኑ መረዳት ይችላል። የኀዳና ፌስቲቫሎች ጥምቀት፣ መስቀል፣ ጨምበላላ እና ሌሎችም ልዩ ልዩ ባሕላዊና ሃይማኖታዊ ሥርዓቶቻችን የተመለከተ የአገሪቱን ሕዝቦች ቁልጭ አድርጎ የሚያሳዩ መሆናቸውን ይገነዘባል። እነዚህን ሃብቶቻችን ማኅበረሰቡ ከበርካታ ሺ ዘመናት በላይ ሳይበረዙና ሳይጠፉ ጠብቆ ለአዲሱና መጪው ትውልድ ማስተላለፍ ችሏል።

የዝግጅት ክፍላችን በዛሬው አገርኛ ዓምድ ላይ በዓለም ቅርስነት ከተመዘገቡት መካከል አንዱ የሆነውን የኮንሶ ባሕላዊ እሴቶችን የተመለከተ ዳሰሳ ይዞ ቀርቧል። ኮንሶዎች በዘጠኝ የጎሳ ድምር ውጤት የተገነቡ፣ በሦስት ተፈጥሯዊ የመሬት አቀማመጥና ባሕላዊ አስተዳደራዊ ሥርዓት የታጠሩና (ቲንባ ካራታ ካታና፣ ከና ቁፋ እና ቱሮታ ቲቲባ) ተብሎ የጥንት ባሕላዊ አስተዳደራዊ ሥርዓት ባለቤት የሆነ ሕዝብ ነው።

በዚህ ውስጥም ኢትዮጵያዊ የሆኑ፣ በሌላ በየትኛውም የዓለም ክፍል የማናገኛቸው ድንቅ የተፈጥሮ አጠባበቅ ጥበብ፣ የደስታና የኃዘን ሥርዓቶች ይገኛሉ። እኛም የኮንሶ ባሕላዊ፣ ተፈጥሯዊ ሃብቶች በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡበትን ምክንያትና እሴቶቹን አጉልተው የሚያሳዩ ባሕላዊ ሃብቶቹን እንደሚከተለው እናቀርባለን። መረጃውን ያደረሱን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ ኃላፊ አቶ ሠራዊት ዲባባ ናቸው።

**ኮንሶ - «አፋ ኾንሶ«**

የኮንሶ ማኅበረሰብ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታታሪና ሥራ ወዳድ ሕዝብ ያለበት አካባቢ እንደሆነ በርካቶች ይመሰክሩለታል። ይህ ታታሪነቱ ከጊዜ ጋር የመጣ ሳይሆን ከቀደሙት ጥንታዊ አባቶቹ የወረሰው ፀጋ መሆኑንም ይናገሩለታል። “ኮንሶዎች ሥራ ይወዳሉ” በሚል ቃል ሁሉም በአንድነት ይስማማል። ከባድ የሚባል ሥራ ለኮንሶ ማኅበረሰብ ሎሚ የመላጥ ያህል ቀላል ነው። ባሕላዊ ዕሴቶች ግንባታ ካልሆነ በቀር በማኅበረሰቡ በፆታ የተከፋፈለ የሥራ መደብ እምብዛም አይስተዋልም። ሴቶች ለኢኮኖሚያዊ ለውጥ ከወንዶች እኩል የመሥራት ባሕል በኮንሶ የተለመደ ነው።

እንደ ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ ኃላፊ አቶ ሠራዊት ዲባባ ገለፃ፤ የኮንሶ ብሔረሰብ “አፋ ኾንሶ” የሚሰኝ የቋንቋ ባለቤት ሲሆን ከምስራቃዊ ቆላማው ኩሽ ቋንቋ ቤተሰብ ይመደባል፡፡ የብሔረሰቡ ቋንቋ ኮንስኛ “አፋ ኾንሶ” ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት መማሪያና በሥነ ጽሑፍ ዝግጅትና ቋንቋነት እያገለገለ የሚገኝ ነው፡፡

“በ2 ሺህ 22 ስኩዌር ኪሎ ሜትር በላይ የቆዳ ስፋት ያለው ኮንሶ ዞን የመሬቱ አቀማመጥ በአብዛኛው ወጣ ገባና ተራራማ ሲሆን አለትና ቋጥኝ ተፈጥሯዊ ሥነ አቀማመጡ ተፈጥሯዊ ፀጋው ናቸው” የሚሉት አቶ ሠራዊት፤ ከፍታውም ከባሕር ወለል በላይ ከ570 እስከ 2 ሺህ 100 ሜትር ከፍታ ላይ እንደሚገኝ ይገልፃሉ፡፡ የሕዝቡ ኢኮኖሚ መሠረቱ በጥምር ግብርና ላይ የተመሠረተ ሲሆን እንስሳት እርባታና ድለባ፣ የንብ ማነብ፣ ዕደ ጥበብ ሥራዎች፣ ማዕድን ክምችት፣ ንግድና የቱሪዝም ገቢ ኢኮኖሚውን የሚደግፉ ተግባራቶቹ ናቸው፡፡ በታሪክና ባሕል አንቱታን ያተረፈ ሕዝብ ከመሆኑም ባሻገር የኮንሶ ሕዝብ የራሱ ብቻ የሆኑ በርካታ የታሪክና የባሕል እሴቶችም አሉት። ከዚህ እንደሚከተሉት የሚቀርቡት ባሕላዊ ሃብቶች የኮንሶ ብቻ የሆኑ አገር በቀል ባሕላዊ ሃብቶች ናቸው።



**የኮንሶ ማኅበረሰብ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባሕል ድርጅት (ዩኔስኮ) ከተመዘገበው ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ ታሪካዊ ቅርሶቹ ባሻገር አያሌ እሴቶች ያሉት ሕዝብ ነው**

**ባሕላዊና ሃብቶች**

የኮንሶ ማኅበረሰብ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባሕል ድርጅት (ዩኔስኮ) ከተመዘገበው ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ ታሪካዊ ቅርሶቹ ባሻገር አያሌ እሴቶች ያሉት ሕዝብ ነው። በስፍራው ሲገኙ ታይተው የማይጠገቡ፣ ተሰምተው የማይሰለቹ የሙዚቃና የጭፈራ ባለቤት ሲሆን ከራሱ ማንነት የሚቀዱ ባሕላዊ አልባሳት፣ የአመጋገብ ሥርዓት ባለቤት ነው። በኮንሶ እንኳን ደስታና ፌሽታ ኃዘንም ይደምቃል። ከእነዚህ ውብ እሴቶቹ ውስጥ ለዚህ ለዛሬው ርዕሰ ጉዳያችን ተገቢ ናቸው ያልናቸውን እንደሚከተለው እናቅርብ።

**ሞትን በዘፈንና ጭፈራ የሚረታው ኮንሶ**

ሞት በኮንሶ ይሸነፋል። ኃዘን ያለና የሚጠበቅ ቢሆንም የኮንሶ ማኅበረሰብ ለመላዕከ ሞት እጁን በቀላሉ የሚሰጥ አይደለም። በአካባቢው ማኅበረሰብ ጥሩ ስምና ዝናን ያተረፉ የጎሳ መሪዎች፣ ታዋቂ ሰዎች ከዚህ ምድር ልፋት እረፍትን ሲያገኙ ኮንሶዎች ሥርዓተ ቀብራቸውን አድምቀው ይሸኟቸዋል። የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ ኃላፊ አቶ ሠራዊት ዲባባ ጉዳዩን ከዚህ እንደሚከተለው ያብራሩታል።

ኃላፊው እንደሚሉት የኮንሶ ማኅበረሰብ ሰው በሚሞትበት ሰዓት በዘፈን እና በጭፈራ በደስታ የሚሸኝበት ባሕል አለው። ይህም ባሕልም “ሺሌታ” ይባላል። የኮንሶ ብሔረሰብ ማኅበራዊ ትስስሩን ከሚያጠነክርባቸው እና ኢኮኖሚያዊ አቅሙን ከሚገልጥባቸው ባሕላዊ ክዋኔዎቹ መካከል “የለቅሶ ሥርዓት” ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል። ባሕላዊው የለቅሶ ሥርዓት የብሔረሰቡ ልዩ ልዩ ባሕላዊ እና ሃይማኖታዊ እሴቶች የሚታዩበት ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፉበት መንገድ ነው።

“የሞተ ሰው አስከሬን ወደ ሚቀበርበት በሚወሰድበት ጊዜ በዘፈን እና ጭፈራ ታጅቦ ይሸኛል” የሚሉት ኃላፊው፤ ከቀብር ሥነ ሥርዓቱም በኋላ ዘፈኑ እንደሚቀጥል ይናገራሉ። በዚህ የዘፈን ስንኞች ውስጥም ስለሞተው ሰው ደግነት፣ በሕይወት እያለ ስላከናወናቸው መልካም ሥራዎች በማንሳት እንደሚሞገስ ይገልፃሉ። የትውልድ ዘር ሐረጉም ተቆጥሮ በክብርና በሞገስ እንደሚዘከር ነው የሚያብራሩት።

“በዘፈን የሚሸኙ ሰዎችም፣ ‘የተመረቁ ሰዎች ናቸው” ተብሎ ይታመናል የሚሉት የኮሙኒኬሽን መምሪያ ኃላፊው፤ እነዚያም ዘፈኖች የተለያየ ግጥም እንዳላቸው ይናገራሉ። ይሁን እንጂ ዘፈኑ የሚዘፈንበት ቆይታ የተለያየ መሆኑን ያብራራሉ። የኮንሶ ማኅበረሰብ ሕይወት ከእርሻ ጋር የተያያዘ በመሆኑ፣ እርሻ በሚታረስበት ወቅት የሞተ ሰው የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ከተከናወነ በኋላ የዘፈን ሥርዓቱ አመቺ ነው ወደሚባሉት ወራት መስከረም ወይም ጥቅምት እንደሚተላለፍ ይገልፃሉ። አረም በሚታረምበት ወቅት ለሞተ ሰው ደግሞ የዘፈኑ ጊዜ ለጊዜው እንዲቆይ እንደሚደረግም ነው የሚያስረዱት።

**ባሕላዊ የስፖርት ጨዋታዎች**

ኮንሶ የባለ ብዙ ዕሴት ባለቤት ነው። ከእነዚህ ውስጥ በማኅበረሰቡ ልዩ ስፍራን የሚሰጣቸው ስፖርታዊ ጨዋታዎች አግራሞትን የሚጭሩ፣ የሚናፈቁና የሚወደዱ ባሕላዊ፣ ታሪካዊና ስፖርታዊ ጨዋታዎች በኮንሶ ብሔረሰብ ይገኛሉ። ከእነዚህ ዕሴቶች መካከል የሚከተሉት የኮንሶ ሃብቶችን ለመመልከት እንሞክር።

**የሶታ ጨዋታ**

“በወንዶች ወጣቶች ብቻ እና ታዳጊዎች ከአቻዎቻቸው ጋር በመግጠም ወኔያቸውን፣ ጥንካሬያቸውን የሚፎካከሩበት ምሽት ከ11 ሰዓት በኋላ የሚጫወቱት ባሕላዊ ስፖርትና ጨዋታ ሶታ ይባላል” የሚሉት አቶ ሠራዊት፤ ሶታ አሸናፊና ተሸናፊ ያለው በሁለት አቻዎች መካከል የሚገጥሙት ባሕላዊ የስፖርት አይነት መሆኑን ይናገራሉ። አሸናፊዎች በትውልድ ዘንድ አይረሴ አሻራ አኑረው የሚያልፉበት ተወዳጅ ጨዋታም መሆኑን ይገልፃሉ። ሶታ በወጣቶችና ታዳጊዎች መካከል የሚኖር ጥንት የነበረ ዛሬም ያለ ነገም የሚኖር የኮንሶ ብሔረሰብ ተወዳጅ ባሕላዊ ጨዋታና ስፖርት ነው፡፡

**የኩራይሳ ስፖርታዊ ጨዋታ**

ሌላው በኮንሶ ማኅበረሰብ ተወዳጅ የሆነው ስፖርታዊ ጨዋታ “ኩራላይ” ይባላል። ተወዳጅ፣ ተናፋቂ፣ ወቅት ጠባቂና የኮንሶ ብሔረሰብ የሆነ ስፖርታዊ ጨዋታ ነው። ጨዋታው በኮንሶ ብሔረሰብ በበጋ ወቅት ወርሐ ጥር እስከ የካቲት መጨረሻ ብቻ የሚካሄድ አይነት ነው። በሁለት የተፈጥሮ ጎራ የተከፈለና እልህ አስጨራሽ ጨዋታው በ"ኩስታና ቃርታ" ወይንም በታናሽና ታላቅ መካከል የሚካሄድ ታላቅ ፉክክር ያለበት ወቅቱን የሚጠብቅ ስፖርታዊ ጨዋታ ነው። "ኩራይላ" ለኮንሶ ማኅበረሰብ የብቻው ስፖርታዊና ባሕላዊ ዕሴት ሲሆን የጨዋታው ስያሜ ከማጫወቻው ኳስ መሰል ድቡልቡል ሉል አግኝቷል። የጨዋታው ሂደት ኳስ መሰሏን ድቡልቡል ሉል ወደ ሰማይ በመወርወር የሚጫወቱት ጨዋታ አይነት ሲሆን ሁለቱ ተጋጣሚዎች ታናሽና ታላቅ ቡድን በአየር ላይ ኳሷን ቀልቦ በመያዝ ነው። መሬት ብትወድቅ እንኳ በትግልና ጥበብ ያሸነፈ ኳሷን ይዞ እጁን ወደ ሰማይ ከፍ በማድረግ "ኦርሶ! አና አላዋ ካሪቴ... አታይቴ፣ ..." በሚል የጀብድነት ማብሰሪያ በእህቱ አሊያም በጎሳው አባል በመማል ኳሷን መያዙን ያረጋግጣል። የዚህን ጊዜ ነው በዙሪያው የከበበው ተመልካች የማን ቡድን ያዘ የሚል ማረጋገጫ የሚሰጡት።

እንደ ኮሙኒኬሽን ኃላፊው ገለፃ፤ በጨዋታው አሸናፊ ሊሆን የሚችለው ቡድን በተከታታይ አምስት ጊዜ ኳሷን የያዘ ቡድን ሲሆን፤ በመሐል ተቃራኒ ቡድን ኳሷን ከያዘ ውጤቱ ከዜሮ ይጀምራል። አንዱ ቡድን በተከታታይ አምስት ነጥብ ባስቆጠረ ጊዜ ደማቅ፣ ሞራላዊና ድል ማብሰሪያ ጭፈራና ቀረርቶ ደጋፊን ጨምሮ ይጫወቱታል። ሴቶች ለጎሳቸው አባል እና ለታናሽና ታላቅ ወንድሞቻቸው ደማቅ ሞራል የሚለገሱ ሲሆን ለአሸናፊና ኳሷን በተደጋጋሚ ይዞ የውጤት ጣሪያ አምስት ነጥብ ከደረሰ ለቡድኑ ከአንገቷ ማጌጫ ጨሌዋን አውልቃ ለአንደኛው አሸናፊ አንገቱ ላይ ታደርጋለች።

**ታኬካ (ታሻ)**

የኮሙኒኬሽን ኃላፊው አቶ ሠራዊት ካደረሱን መረጃዎች ውስጥ የሆነውና ሌላኛው ስፖርታዊ ጨዋታ ታኬካ (ታሻ) ተብሎ ይታወቃል። ይህም በኮንሶ ለአባቶች እና ጎልማሶች በአመዛኙ የሚጫወቱት ባሕላዊ ጨዋታ ሲሆን፤ ፈለገ ሂሳብ ያለው እንደሆነ ገልፀውልናል። ጨዋታው ማስተዋልን የሚጠይቅ፣ (በሞራ) ባሕላዊ መሰብሰቢያ አደባባይ ብቻ የሚገኝ የኮንሶ ብሔረሰብ ባሕላዊ ጨዋታ ነው፡፡ ታኬካ በማስተዋልና ጥበብ የሚጫወቱት ጨዋታ ሲሆን፤ ጨዋታውን ከአባቶችና ጎልማሶች አልፎ አልፎም ወጣቶች ይጫወቱታል። ይህ ባሕላዊ ስፖርት አይነት "በዘመናዊ አጠራሩ ገበጣ" ሲሆን በኮንሶ ማኅበረሰብ ባለ 6፣ ባለ 12 ታሻ የሚል ሂሳባዊ ቀመር ያለው ነው።

**እንደ መውጫ**

የኮንሶ ማኅበረሰብ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባሕል ድርጅት (ዩኔስኮ) የተመዘገበው ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ ታሪካዊ ቅርሶቹ የሚዘክር በዓል በየዓመቱ ሰኔ 23 ቀን ያከብራል። በአገሪቱና በዞኑ በቅርቡ በተከሰተ የፀጥታ ችግር ምክንያት ለአራት ተከታታይ ዓመታት ሳይከበር ቆይቷል። የኮንሶ ዞን አስተዳደር ዘንድሮ ይህን ዓመታዊ በዓል እንደሚያከብር አስታውቋል። ይህንን ጉዳይ አስመልክተው ይፋዊ ቃል የሰጡት የኮንሶ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ዳዊት ገበየሁ እንዳሉት፤ የኮንሶ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ቅርሶች በዓለም ደረጃ ታዋቂ ነው። ታታሪው የኮንሶ ሕዝብ በዓለም እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ የቅርስ አካል በሆነው የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ፣ የእርከን ሥራ እንዲሁም የተፈጥሮ የኮንሶ መልክዓ ምድር አቀማመጡ በሰው የሠራሽ የካብ ጥበብ ዓለም የመሰከረለት ቅርስ ላለፉት አራት ዓመታት ሳይከበር የቆየው የኮንሶ መልክዓምድር ጥበቃና ባሕል ዩኔስኮ በዓል ቀን ከቀናት በኋላ ለማክበር ዝግጅቶች ተጠናቀዋል።

# ወጣቶች

## ‹‹የሕዋ ሳይንስ ቅንጦት አይደለም››

**- የሕዋ ሳይንስ ተመራማሪው ወጣት ትንሳኤ ዓለማየሁ**

**ክብረአብ በላቸው**



ወጣት ትንሳኤ ዓለማየሁ ይባላል። ውልደቱ በመዲናችን አዲስ አበባ ነው። ዕድገቱ ደግሞ በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች ሲሆን፤ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን ጄኔሬሽን 2000 በተባለ ትምህርት ቤት ተከታትሏል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ አቡነ ጎርጎርዮስ ተምሯል። በትምህርቱ ጎበዝ ከሚባሉ ተማሪዎች መካከል የነበረው ትንሳኤ፤ በ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ጥሩ ውጤት በማስመዝገብ ለከፍተኛ ትምህርት መቀሌ ዩኒቨርስቲን ተቀላቅሏል።

ከልጅነቱ ጀምሮ ለሕዋ ሳይንስ ልዩ ፍቅር ስለነበረው ለዚህ ይረዳው ዘንድ ለዘርፉ ይቀርባል ያለውን የሜካኒካል ምሕንድስና ትምህርት ክፍል መርጦ በመቀላቀል ትምህርቱን እስከ አምስተኛ ዓመት መጨረሻ ድረስ ተከታትሏል። ለተግባር ልምምድ አዲስ አበባ በነበረበት ወቅት በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል አጋጥሞ በነበረው ጦርነት ምክንያት ወደ መቀሌ ተመልሶ ትምህርቱን ማጠናቀቅ አልቻለም፤ በዚህም የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ቆይታው እስከ መጨረሻው አልዘለቀም።

የትምህርት ሚኒስቴር በትግራይ ክልል በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸው ሲከታተሉ የነበሩ ተማሪዎችን ወደ ተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች በማስቀየር ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ሲያደርግ ወጣት ትንሳኤ ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ደረሰው። በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የቀሩ ኮርሶችን፣ በተግባር ልምምድ የሠራቸውን ሥራዎች እና የመመረቂያ ጽሑፍ በማቅረብ ማጠናቀቅ ቻለ። ዩኒቨርሲቲው በወቅቱ ስለእነርሱ መረጃ ስላልነበረው ማስመረቅ እንደማይችል በመግለፅ፤ የሁለተኛ ደረጃ ሰርተፍኬት ብቻ ሰጥቶ ሸኘው።

አሁንም ድረስ የትምህርቱ ጉዳይ በዚሁ መንገድ ዕልባት ሳያገኝ ቢቆይም፤ አሁን ወደ ቀድሞ ሰላም መመለስ በመቻሉ የትምህርቱ ጉዳይ መቋጫ ያገኛል የሚል እምነት እንዳለው ወጣት ትንሳኤ ይናገራል።

በወቅቱ እርሱ በግሉ በውጭ ሀገር ትምህርቱን ለመከታተል የተለያዩ የትምህርት ዕድሎችን ይሞክር ነበር። ሙከራው ተሳክቶለት በውጭ የሚሰጡ ኮርሶችን ለመማር ከሀገር ውጭ በመጓዝ ትምህርቱን ተከታትሏል።

ወጣት ትንሳኤ ከአውሮፓውያኑ 2012 ጀምሮ የኢትዮጵያ የጠፈር ሳይንስ ማኅበረሰብ አባል ሲሆን፤ በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ቆይታውም በኢትዮጵያ የጠፈር ሳይንስ ማኅበረሰብ የመቀሌ ቅርንጫፍ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ሆኖ ሠርቷል። በተባበሩት መንግሥታት የሕዋ ሳይንስ ድጋፍ በሚደረግለት ስፔስ ጄኔሬሽን አድቫይዘሪ ካውንስል በተባለው እና ወጣቶችን የማስተሳሰር ሥራ በሚሠራው መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ውስጥ ከአውሮፓውያኑ 2013 ዓ/ም ጀምሮ የኢትዮጵያ አስተባባሪ በመሆን ሠርቷል።

ከልጅነት ጊዜው ጀምሮ ለሕዋ ሳይንስ ምርምር እና ለምሕንድስና ሙያ ከፍተኛ ፍላጎት እንደነበረው የሚናገረው ወጣት ትንሳኤ፤ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ከነበረበት ጊዜ አንስቶ የኢትዮጵያ የሕዋ ሳይንስ ማኅበረሰብ አባል በመሆን ከመደበኛ ትምህርቱ በተጓዳኝ በንባብ ያገኘውን የኅዋ ሳይንስ ዕውቀት ለሌሎች ለማካፈል ሥልጠናዎችን ሲሰጥ ቆይቷል።

‹‹መሠረታዊ በሆኑ ነገሮች ላይ ብዙ የሚቀረን ነገር አለ›› ብሎ የሚናገረው ይኸው ወጣት አብዛኛዎቹ ሥራዎቹ በግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች ላይ ያተኮሩ ነበሩ። ወጣት ትንሳኤ፤ በዚህም ምክንያት በአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች፣ በአጠቃላይ ሕዝቡ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን በስፋት ይሠራ እንደነበር ተነግሯል።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጅማሮው አካባቢ ለዘርፉ ፍላጎቱ እየጨመረ እንደመጣ እና የታሪክ መጽሐፍትን፤ የብራና ጽሑፎችን ለመዳሰስ በሚሞክርበት ወቅት ኢትዮጵያ በዘርፉ ያላትን ነገር በተወሰነ መልኩ ማየት እንደቻለ እና በባሕርይ ብዙ ያልተዳሰሱ ሐሳቦችን ማየት ስለሚወድ ትኩረቱን እንደሳበው ይናገራል። ነገር ግን በሕዋ ሳይንስ የበለጠ እንዲሳብ ያደረገው የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ በነበረበት ወቅት የፊዚክስ መምህሩ እንደሆኑ ወጣት ትንሳኤ ወደኋላ ተመልሶ ያስታውሳል።

የኢትዮጵያ ስም በታሪክ፣ በሕክምና እንዲሁም በሌሎች ዘርፎች ሊነሳ ይችላል። በሕዋ ዘርፍ ግን ብቅ ማለት የተጀመረው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው የሚለው ወጣት ትንሳኤ፤ የብራና መጽሐፍት ላይ የድሮ አባቶች በጊዜው በነበራቸው አረዳድ የሕዋ ሳይንስን የተረዱበት መንገድ ያስደንቀው እንደነበር እንዲሁም እርሱን ከሌሎች በዘርፉ ከተሰማሩ ግለሰቦች ለየት የሚያደርገው በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ የተነሳ ብቻ ሳይሆን የታሪክ ጥናት ወደ እዚህ ዘርፍ ያመጣው እንደሆነ ይገልፃል።

እ.ኤ.አ በ2019 ዓ.ም በአፍሪካ ደረጃ በየዓመቱ የሚዘጋጀውን ሦስተኛውን የአፍሪካ የሕዋ ሳይንስ ዐውደ ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ እንዲዘጋጅ እንዳደረገ እና የእርሱን ተስፋ ሰጪ ሥራዎች የተመለከቱ አፍሪካ ኢን ስፔስ የተባለው ተቋም ባካሄደው የ2021 የአፍሪካ ወጣት ምርጥ የሕዋ ሳይንስ ተመራማሪዎች ምርጫ ዕጩ ሆኖ ቀርቦ ከበርካታ የአፍሪካ ሀገራት የተወከሉ ተወዳዳሪዎች በተሳተፉበት ውድድር ወጣት ትንሳኤ ከአፍሪካ 10 ምርጥ የሕዋ ሳይንስ ተመራማሪ ወጣቶች ዝርዝር ውስጥ መካተት ችሏል።

በወቅቱ እውቅናው ከዚህ ቀደም ለተሠሩ ሥራዎች ዋጋ ከመስጠቱ ባሻገር በዓለም አቀፍም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወደ ፊት ለሚሠራቸው ሥራዎች በር ከፋች በመሆኑ አስተዋፅዖው ትልቅ እንደነበር ይናገራል። በተጨማሪ አንድ ሰው ወደዚህ ዘርፍ ሲመጣ በብዛት በመጀመሪያ የሚጠየቀው በዚህ ዘርፍ ምን ሠርተሃል? ምን አይነት ልምድ አለህ? የሚል ነው። እንዲህ አይነት ዕውቅና ደግሞ የወደፊት እቅዶቹ ለማሳካት በር ከፋች ናቸው ብሎ እንደሚያስብ ወጣት ትንሳኤ ይነገራል።

በቱርክ ሀገር የአቪየሽን ቴክኖሎጂ ሥልጠናን የተከታተለው ትንሳኤ፤ የመቀሌ እና የቤልጅየሙ ቶማስ ሞር ዩኒቨርሲቲዎች በጋራ ባዘጋጁት ሙን ሹት ኢትዮጵያ የተባለ ልዩ የትምህርት መርሐ ግብር ተከታትሎ የድርብ ክብር ዲግሪ አግኝቷል። ለዘርፉ ተመራማሪዎች በሚሰጠው ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድጋፍ መርሐ ግብር እ.ኤ.አ 2021 ዓ.ም አሸናፊ ከሆኑ ከአምስት የሕዋ ሳይንስ ተመራማሪዎች ውስጥ ከአፍሪካ የመጀመሪያው መሆን ችሏል።

ታሪክና ጥንታዊ መጽሐፍትን ማንበብ ያዘወትር እንደነበር የሚነገርለት ወጣት ትንሳኤ፤ ተወልዶ ባደገባት አዲስ አበባ ከተማ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በተከታተለበት የአቡነ ጎርጎሪዮስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የግዕዝ ቋንቋ መማሩ ደግሞ ተጨማሪ ጥንታዊ መጽሐፍትን ለማገላበጥ ዕድል እንደሰጠው እና ከእነዚህ መጽሐፍት ያነበበው ጥንታዊ ታሪክ የሕዋ ሳይንስ ምርምር የበለፀጉ ሀገራት ብቻ ሳይሆን፤ ኢትዮጵያ ውስጥም ጥንታዊ መሠረት እንዳለው እንዲገነዘብ እንዳደረገው፤ ይህም በትምህርት ቤት ከሚያገኘው ዘመናዊ የሳይንስ ትምህርት ጋር ተደምሮ ወደ ሕዋ ሳይንስ ምርምር የበለጠ እንዲሳብ እንዳደረገው ተነግሯል።

ስድስተኛ ክፍል ተማሪ ሆኖ አቡነ ጎርጎርዮስ ትምህርት ቤት ሲገባ፤ ግዕዝ መማር እንደጀመረ እና ትምህርት ቤቱ ውስጥ ስለሚሰጥ በዚያ ምክንያት ያነባቸው የነበሩ መጽሐፍት ከአማርኛ መጽሐፍት በተጨማሪ የግዕዝ እና የብራና መጽሐፍትን የማንበብ አቅምን እንደፈጠረለት ገልፆ፤ ካነበባቸው ጥንታዊ መጽሐፍት ውስጥ በተለይ አንዱ የበለጠ ለዘመናዊው የሕዋ ሳይንስ ቀረቤታ እንደነበረው ወጣት ትንሳኤ ያስታውሳል።

በተለይ አክሲማሮስ የሚባል አንድ መጽሐፍ ነበር የሚለው ትንሳኤ፤ በመሠረቱ መጽሐፉ ስለ ሥነ-ፍጥረት የሚያወራው ነበር። ነገር ግን እዛ ላይ ስለ ሥነ-ፍጥረት ሲያወራ ሕዋው እንዴት እንደተፈጠረ የሚያብራራበት መንገድ ከሳይንሱ ጋር በአገላለፅ ደረጃ ተመሳሳይነት ስለነበረው እና በተወሰነ መጠን ደግሞ እርሱ በሳይንስ ከሚያውቀው ነገር ጋር ለማገናኘት ሲሞክር መመሳሰሎች ስለነበሩት ይህ በእጅጉ ቀልቡን የሳበው ጉዳይ እንደነበር ወጣት ትንሳኤ ተናግሯል።

ትንሳኤ እንደሚለው በኢትዮጵያ የሕዋ ሳይንስን በንድፈ-ሃሳብ ደረጃ የሚረዱ በርካታ ልጆች አሉ። ነገር ግን ከሳይንሱ በስተጀርባ ያለውን እውነታ በተግባር በተደገፈ ትምህርት እንዲረዱ ማድረግ ላይ ብዙ አልተሠራበትም ይላል። ይህንን ለመቅረፍ በቅርብ ከሚገኙ ቁሳቁሶች የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በመሥራት በተግባር ትምህርቱን እንዲቀስሙ ቢደረግ ውጤታማ ተመራማሪዎችን ማፍራት እንደሚቻል ይገልፃል። የሕዋ ሳይንስ ዕውቀቱን ለሌሎች ለማካፈል ሥልጠናዎችን ይሰጥ በነበረበት ወቅትም ይህንኑ መንገድ ይከተል እንደነበር ይናገራል።

የሕዋ ሳይንስ ከዕለት ተዕለት የሰዎች ሕይወት ጋር የተሳሰረ እንጂ፤ የቅንጦት እና ለበለፀጉ ሀገራት ብቻ የተሰጠ አይደለም የሚለው ወጣት ትንሳኤ፤ የሕዋ ሳይንስም እንደማንኛውም ዕውቀት ሀብት በመሆኑ ኢትዮጵያም ልትጠቀምበት እንደሚገባ ይገልፃል። ለበለፀጉ ሀገራት እንጂ ለእንደኛ አይነት ታዳጊ ሀገራት የሕዋ ምርምር አይሆንም ማለት እንደማይቻል ያስረዳል። ያለ ሕዋ ሳይንስ የግብርና፣ የትምህርት፣ የጤና ዘርፎችን ማዘመን እንደማይቻል ይገልፃል። ስለዚህ እነዚህን ነገሮች ለማዘመን፤ ለዘርፉ ትኩረት መስጠት ለነገ የሚባል እንዳልሆነም ተነግሯል።

ዘንድሮ ባሳለፍነው ሳምንት መጀመሪያ ወደፊት የሕዋ ምርምር ዘርፍ ይመራሉ ብሎ የዓለም የሕዋ ምርምር ፌዴሬሽን በዓለም አቀፍ ደረጃ ከመረጣቸው አምስት ወጣት ተመራማሪዎች አንዱ እና በታሪክ በ25 ዓመቱ ይህንን ሽልማት ያገኘ በዕድሜ ትንሹ ሰው መሆን የቻለው ወጣት ትንሳኤ፤ ስለዚህ ጉዳይ ሲናገር አራቱ ግለሰቦች እውቅ በሆኑ የሕዋ ተቋማት የሚሠሩ ናቸው። እርሱ ደግሞ ከአፍሪካ ብቸኛ ሆኖ መቅረቡ እንደ ሀገር ለኢትዮጵያ እንደ አህጉርም ደግሞ ለአፍሪካ ፋይዳው ትልቅ እንደሆነ ገልጿል።

የሕዋ ሳይንስ በየትኛውም ዘርፍ ላይ ያለን ሰው የመቀበል አቅም አለው የሚለው ወጣት ትንሳኤ ጋዜጠኛ፣ ሐኪም፣ ወይም መሐንዲስ በሙያው ለዘርፉ ድጋፍ ማድረግ ይችላል። የሕግ ባለሙያዎች እንኳ በሕዋ ሕግ መገልገል ይችላሉ። የአንድ መሥሪያ ቤት ሥራ አስኪያጅ፣ የቢሮ ባለሙያ፣ ጥበቃ፣ የፅዳት ባለሙያ እንደሚፈልገው ሁሉ፤ ሕዋ እንደ ሴክተር ያለ በመሆኑ የሁሉንም ሙያ ባለቤቶች ይፈልጋል የሚለው ተመራማሪው፤ ስለዚህ ወጣቶች በሕዋ ዘርፍ ላይ መሰማራት ቢፈልጉ ያላቸውን ሥራ ሳይለቁ የራሳቸውን አበርክቶ ማኖር ይችላሉ ብሏል።

‹‹እንደ ወጣት ኃላፊነት ሊሰማን ይገባል፤ እኛ የምንሠራው ለእራሳችን ብቻ መሆን የለበትም›› የሚለው ትንሳኤ፤ ቀጣይ ትውልድ የተቃና ሕይወት እንዲኖረው ለማድረግ ጥረት ማድረግ የወጣቶች ኃላፊነት መሆኑን ይናገራል። የነገዋን ኢትዮጵያ ለመገንባት ዛሬ ለመሥራት ወጣቶች በቁርጠኛነት የመንቀሳቀስ ግዴታ እንዳለባቸውም ያመለክታል።

‹‹ዓለም የሕዋ ሳይንስ ባበረከተው ፈጠራ ላይ ጥገኛ ናት።››፤ የገንዘብ መቀበያ ማሽን፣ የሕክምና፣ የስልክ፣ የቴሌቪዥን እና መሰል በዕለት ተዕለት ሕይወታችን የምንጠቀምባቸው ነገሮች የሕዋ ሳይንስ ውጤቶች ናቸው፤ ኢትዮጵያ ይህንን አገልግሎት ሁሉ የምታገኘው በውጭ ምንዛሪ ከሌሎች ሀገራት በክፍያ ነው። እንደ ሀገር የፈጠራው አካል ብትሆን ወጪ ከማስቀረት አልፋ ገቢ የምታገኝበት ዘርፍ መሆን ይችላል፤ ስለዚህ ወደዛ ለመምጣት ኢትዮጵያ እራሷን ማብቃት መቻል እንዳለበት ወጣት ትንሳኤ ተነግሯል።

የሕዋ ሳይንስ ከሁሉም በበለጠ የሚያስፈልገው ለአፍሪካ ነው፤ አፍሪካውያንም በሕዋ ምርምር የላቀ ደረጃ የመድረስ አቅም አላቸው የሚለው ወጣት ትንሳኤ፤ በአሁኑ ወቅት በደቡብ አፍሪካ በሚገኝ ኪውስርየስ በሚባል የሳተላይት መቆጣጠሪያ ተቋም ውስጥ እየሠራ ይገኛል። ይህ ተቋም በዘርፉ በዓለም ላይ አሉ ከሚባሉ ተቋማት መካከል አንዱ እንደሆነ ገልፆ፤ አፍሪካዊ ድርጅት በመሆኑ ለሥራው ፍቃደኛ ሆኖ ስለመቀላቀሉ ተናግሯል። አፍሪካ ውስጥ የእስፔስ ቢዝነስ ማሳደግ ይቻላል የሚለው ወጣት ትንሳኤ፤ ከእርሱ መርሕ አንፃር አሁን ያለበት ተቋም ለአህጉሪቱ የሕዋ ሳይንስ እድገት በሚያበረክተው አስተዋፅዖ የድርሻውን ሚና ለመጫወት ጥረት እንደሚያደርግም ተናግሯል።

ወጣት ትንሳኤ የወደፊት ዕቅዱን እና ምን ማሳካት እንደምፈልግ ሲናገር፤ የሕዋ ሳይንስ ባለሙያ የመሆኑ ሐሳብ ስላለው በተለያየ ዘርፍ ዕውቀት እንዲኖረው ይሻል። ምክንያቱም ዘርፉ በጣም ሰፊ ስለሆነ ጠቅላላ ዕውቀት ይፈልጋል። በዚህ ምክንያት ትምህርቱን አጠናክሮ እንደሚቀጥል እና በዘርፉ ጥሩ ዕውቀት ይዞ ወደ ሕዋ ኢንዱስትሪው ተቀላቅሎ መሥራት እንደምሚፈልግ ገልጿል። አገሩን ኢትዮጵያን በሕዋ ምርምር የሚያስጠራ እና ከዘርፉ ተጠቃሚ የሚያደርገውን ሥራ በተግባር መሥራት እና ማበርከት እንደሚፈልግ ገልፆ፤ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ብሎም በአፍሪካ እንዲሁም በዓለም በብዙ ዘርፎች ላይ የሚሠራ የሮስፔስ ተቋም እንዲኖረው እንደሚፈልግም ተነግሯል። ወጣት ትንሳኤ ለደረሰበት ስኬት ለወላጆቹ እንዲሁም ለሠራባቸው እና ለተማረባቸው ተቋማት ትብብር ከፍ ያለ ምስጋናውን ያቀርባል።

# የምድር በረከት

# መሻሻል እያሳየ የመጣው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የወርቅ ግብይት

ወርቅነሽ ደምሰው

መንግሥት እንደ አገር ወደ ብሄራዊ ባንክ ለሚገባው የወርቅ መጠን እየቀነሰ መምጣት ምክንያት የሆኑትን ችግሮች በጥናት በመለየት ለመፍትሄው እየሰራ ይገኛል። በወርቅ ግብይት ላይ ለተፈጠረው ችግር ዋናው ምክንያት በወርቅ ፍለጋ፣ ማምረትና ግብይቱ በህገወጦች ከፉኛ መያዙ መሆኑን በመረዳት ህገወጥ ድርጊቱን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ እርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል። እርምጃው እየተወሰደባቸው ከሚገኙ ክልሎች መካከል በወርቅ ማእድንና ምርቱ በእጅጉ የሚታወቀው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አንዱ ነው።

በክልሉ በመንግሥት በተወሰደ እርምጃ በርካታ የውጭ ዜጎችና ተባባሪዎቻቸው ኢትዮጵያውያን በወርቅ ማእድን ፍለጋ፣ ማምረትና ግብይት ላይ ተሰማርተው በመገኘታቸው በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የጸጥታና ደህንነት ግብረ ኃይል ከወራት በፊት ያወጣው መረጃ ያመለክታል። ግብረ ኃይሉ እንዳለው፤ የፀና የጉዞ ሰነድ፣ የመግቢያ ቪዛ እንዲሁም የመኖሪያ ፍቃድ ሳይኖራቸው በሕገ-ወጥ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ወርቅና የተለያዩ ማዕድናት ፍለጋ እንዲሁም የማምረት ስራ ላይ የተሰማሩ 47 የውጭ አገር ዜጎች በቁጥጥር ስር ውለዋል።

በተመሳሳይም በክልሉ በሕገ-ወጥ የወርቅ ምርትና ግብይት ተግባር ላይ ተሰማርተው የተገኙ 29 የውጭ አገራት ዜጎች እና ሁለት ኢትዮጵያውያን ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን በቅርቡ የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ማስታወቁ ይታወሳል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በወጣ መረጃ መንግሥት በክልሉ በወርቅ ማእድን ህገወጥ ፍለጋ፣ ማምረትና ግብይት ላይ በተሰማሩ የውጭ አገር ዜጎችና ተባባሪዎቻቸው ኢትዮጵያውያን ላይ የወሰዳቸውን እርምጃዎች ተከትሎ ለብሔራዊ ባንክ የሚቀርበው የወርቅ መጠን እየጨመረ መጥቷል። የክልሉ ማእድን ቢሮ ኃላፊ አቶ ካሚል ሀመድ በተለይ ለኢፕድ ሰሞኑን የሰጡት መረጃም ይህንኑ ያረጋግጣል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በበጀት ዓመቱ በአንደኛና በሁለተኛ ሩብ ዓመት የወርቅ ምርትና ግብይት አፈጻጸም በጣም ዝቅተኛ የሚባል ነበር፤ ከመጋቢት ወር ጀምሮ በወርቅ ምርትና ግብይት ላይ በተደረገው ከፍተኛ ቁጥጥር መሻሻሎች እየታዩ መጥተዋል።

ከክልሉ የተገኘው መረጃ እንዳመለከተው፤ ክልሉ በ2014 በጀት ዓመት 2ሺ300 ኪሎ ግራም ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ ገቢ አድርጓል። ይህንን መነሻ በማድረግ በ2015 በጀት ዓመት ሦስት ሺ ዘጠኝ ኪሎ ግራም ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ ገቢ ለማድረግ አቅዶ ወደ ስራ ገብቶም ነበር። እስካሁን ባለው ሂደትም 482 ኪሎ ግራም የሚገመት ወርቅ ተገኝቷል፤ አፈጻጸሙ ግን ካለፈው በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር በጣም ዝቅተኛ ነው።

የክልሉ ማዕድን ቢሮ ኃላፊ አቶ ካሚል ሀመድ ለወርቅ ምርትና ግብይት አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆን ዋነኛው ምክንያት ሕገወጥ የወርቅ ግብይት መበራከት መሆኑን ይገልፃሉ። በተለይ በርካታ የሰው ኃይል በሚሰራባቸው አንዳንድ ካምፖች አካባቢ የወርቅ ምርት ቅነሳ መታየቱ በጥናት መረጋገጡንም ይጠቁማሉ።

ኃላፊው እንዳሉት፤ በቅርቡ በፌዴራል ደረጃ በተቋቋመ ግብረ ኃይል በክልሉ በወርቅ ምርትና ግብይት ላይ በተሰማሩ ሕገወጥ የውጭ ዜጎች ላይ የተወሰደው አይነት እርምጃ ቀደም ሲልም በክልል ደረጃም ሲወሰድ ቆይቷል፤ ክልሉ ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ በእነዚህ የውጭ ዜጎች ላይ እርምጃ በሚወስድበት ወቅት የውጭ አገር ዜጎች ናቸው በሚል የሚሰሙ በርከት ያሉ ጩኸቶች ነበሩ። እነዚህ የውጭ አገር ዜጎች በሚሰሩባቸው አካባቢዎች ወደ ብሔራዊ ባንክ የሚገባ ምንም አይነት ወርቅ አነልነበረም። በዚህ ምክንያት የውጭ አገር ዜጎቹ ተከሰው ጉዳያቸው በፍርድ እየታየ ይገኛል። በሌሎች ባልተያዙ ሕገወጦች የሚወሰደው እርምጃዎቹ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ክልሉ ቀደም ሲልም ጀምሮ በሕገወጥ መንገድ በወርቅ ምርትና ግብይት ላይ የተሰማሩ አካላትን እየተከታተሉ እርምጃዎችን እየወሰደ እንደነበር የጠቆሙት ኃላፊው፤ ጠንከር ያሉ እርምጃዎች በመውሰድ ረገድ ግን ክፍተቶች እንደነበሩም ተናግረዋል። በወቅቱ እንደ አሁኑ ዓይነት ጠንከር ያሉ እርምጃዎች ለመውሰድ የሚያስችሉ



አቶ ካሚል ሀመድ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ማዕድን ቢሮ ኃላፊ

**በሕገወጥ የወርቅ ምርትና ግብይት ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ሰዎች የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም በሕገወጥነት ተግባር ላይ ተሰማርተው ስለተደረሰባቸው እርምጃ ተወስዶባቸዋል**

ሁኔታዎች እንዳልነበሩም አስታውሰው፣ አሁን በፌዴራል ደረጃ ከተቋቋመ ግብረ ኃይል ጋር አቋም በመያዝ የማያዳግም እርምጃ እየወሰድን እንገኛለን ብለዋል።

በክልሉ ወርቅ ለማምረት የሚያስችል አቅም የሌላቸው አንዳንድ በወርቅሥራ ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው አካላት እንዳሉ ኃላፊው ጠቁመው፣ እነዚህ አካላት ወርቅ ለማምረት የሚያስችል ቴክኖሎጂም ሆነ የተማረ የሰው ኃይል እንደሌላቸው ተናግረዋል። በዚህ መሀል የሚፈጠሩ ክፍተቶች ወርቅ በሕገወጥ መንገድ እንዲመረት በር መክፈታቸውንም ጠቅሰው፣ እነዚህ ማህበራት በወርቅ ስራ ላይ መሰማራታቸው እንጂ እምብዛም እውቀቱ እንደሌላቸውም አስታውቀዋል።

‹‹አብዛኛዎቹ የውጭ አገር ዜጎች የወርቅ ቀለምን የሚቀይሩ ኬሚካሎችን ይዘው ነው ወደ አገር ውስጥ የሚገቡት›› የሚሉት ኃላፊው፤ ይህ አይነቱ ሕገወጥነት እዚህ ካለው ማህበረሰብ ንቃት ህሊና አንጻር ሲታይ በእሱ ደረጃ መቆጣጠር የሚቻል አልነበረም ይላሉ። ሕገወጦቹ ቴክኒካል ሥራዎች በመሥራት ህገወጥ ድርጊቱን ሲፈጽሙ መቆየታቸው እንዳልታወቀባቸው ገልጸዋል።

ኃላፊው በሕገወጥ የወርቅ ምርትና ግብይት ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ሰዎች የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም በሕገወጥነት ተግባር ላይ ተሰማርተው ስለተደረሰባቸው እርምጃ ተወስዶባቸዋል ብለዋል። በወርቅ ህገወጥ ተግባር እርምጃ የተወሰደበትን « ኢሊኒት» የተሰኘውን ድርጅት ለአብነት ጠቅሰው ሲያብራሩም፣ ድርጅቱ ሕጋዊ የወርቅ ማምረት ፈቃድ ያለውና ከፍተኛ የወርቅ አምራች ሆኖ በዚያ ልክ ወርቅ ባንክ ሲያስገባ እንዳልነበረ ተናግረዋል። ድርጅቱ በሕገወጥ የወርቅ ምርት ላይ ተሰማርቶ በመገኘቱ ቀደም ሲል እርምጃ ተወስዶበት የወርቅ ማምረት ሥራውን እንዲያቆም ተደርጎ እንደነበርም አመልክተዋል።

ኃላፊው እንዳስታወቁት፤ ሕጋዊ ከሆኑ አነስተኛ ማህበራት ጋር ተቀላቀለው የገቡ ሌሎች ሕገወጦች መኖራቸውም ተደርሶበታል። አምራቾቹ በነበሩበት ሳይት ወርቅ አምርቶ ወደ ብሔራዊ ባንክ እስካልገባ ድረስ የወርቅ ምርቱ የት ገባ የሚለው ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። እነሱ የሚያመርቱት ወርቅ ብሔራዊ ባንክ እስካልገባ ድረስ መድረሻው የት እንደሆነ መቆጣጠር ያስፈልጋል። ቀደም ሲል አብዛኛው ወርቅ በሕገወጥ መንገድ ወደውጪ ይወጣ ነበር። አሁን ሕገወጥነት እየተስፋፋ መጥቶ በህገወጥ መንገድ ከክልሉ የሚወጣው ወርቅ ወደ መሀል አገር ጭምር እየተወሰደ ይገኛል።

‹‹አሁን በክልሉ በወርቅ ምርት ላይ መሻሻሎች እየመጡ ነው›› የሚሉት ኃላፊው፤ በአሁኑ ወቅት በየሳምንቱ እስከ 10 ኪሎ ግራም ወርቅ ለብሄራዊ ባንክ ገቢ እየተደረገ መሆኑን አስታውቀዋል። በተለይ ከመጋቢት ወር 2015 ዓ.ም ጀምሮ መሻሻሎች መምጣቸውን ነው የጠቀሱት፤ የወርቅ ምርትና ግብይቱ በመጋቢት ወር 12 ነጥብ 3 ኪሎ ግራም፣ ሚያዚያ ወር 20 ኪሎ ግራም እና በግንቦት ወር ደግሞ 43 ኪሎ ግራም ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ ገቢ ተደርጓል። ቁጥጥሩ ጥሩ ለውጥ ማምጣት እያስቻለ ነው ብለዋል።

ኃላፊው እንዳብራሩት፤ ብሔራዊ ባንክ በወርቅ ዋጋ ላይ የወሰደው የማሻሻያ እርምጃም በሕገወጦች ምክንያት መቀዛቀዝ ባሳየው የወርቅ ምርትና ግብይት ላይ የተወሰኑ መሻሻሎች ማምጣት እያስቻለ ነው፤ ወደ ብሔራዊ ባንክ የሚገባው ወርቅ በየጊዜው እየጨመረ መጥቷል፤ ለአብነት ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም 5 ነጥብ 9 ኪሎ ግራም ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ መግባቱ እስካሁን ድረስ ባለው ሁኔታ በየቀኑ ይገባ ከነበረው የወርቅ መጠን ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ቁጥር የያዘ ነው። እስካሁን ባለው ሂደት ሰኞ ሰኞ ቀን በአማካይ 5 ኪሎ ግራም ወርቅ ይገኛል፤ እንደ ክልሉ በተለየ ሁኔታ ቅዳሜና እሁድ ተሰርቶ ሰኞ ላይ የተሻለ መጠን ያለው የወርቅ ምርት ለብሔራዊ ባንክ ገቢ ይደረጋል።

በተለይ በባህላዊ መንገድ ወርቅ በማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላትን ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ ገብቶ ለአገር የሚሰጠውን ኢኮኖሚያ ፋይዳ እንዲሁም ወርቅን የጋራ ሀብት መሆኑን በማስረዳት የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ እየተሰራ መሆኑንም ነው ኃላፊው የሚናገሩት።

እንደ ክልል አሁን ባለው ሁኔታ በአንጻራዊነት ሲታይ በባህላዊ መንገድ ወርቅ የሚያመርቱ አካላት በተሻለ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ የሚሉት ኃላፊው፤ አሁን እንደ ክልል ትልቁ ችግር ያለው ኩባንያዎች ጋ መሆኑንም ይገልጻሉ። ኩባንያዎች በወርቅ ማምረት ሥራ ላይ ተሰማርተው የተሻለ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ እንደሚሆኑ ይጠበቃል፤ ይሁንና አሁን ያላቸው አቅም ግን በዚህ ልክ አይደለም ብለዋል። ለምሳሌ እንደ ኢሊኔት ያሉ ኩባንያዎች በሕገወጥነት ሥራ ተሰማርተው በመገኘታቸው ነው እርምጃ የተወሰደባቸው።

በሌላ በኩል ሌሎች በወርቅ ማምረት ሥራ ላይ ለመሰማራት ፍቃድ ወስደው ወደ ሥራ ያልገቡ እንዳሉም ኃላፊው ጠቅሰዋል። በሥራውም ላይ ያሉት በሚጠበቀው ልክ ወርቅ አምርተው ማቅረብ አለመቻላቸውን ገልጸዋል። ይህ ደግሞ በወርቅ ምርቱ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊፈጥር መቻሉን አመላክተዋል።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ በክልሉ በባህላዊ የወርቅ ማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ 370 ማህበራት አሉ፤ ከእነዚህ ውስጥ ይነስም ይብዛም ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ ማስገባት የጀመሩት 30 የሚያህሉት ብቻ ናቸው።

ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ ማስገባት ያለባቸው አምራቾች፣ አዘዋዋሪዎች እና ኩባንያዎች ሲሆኑ፤ አሁን ላይ በወርቅ አዘዋዋሪዎች በኩል ወደ ብሑራዊ ባንክ የሚገባው ወርቅ እዚህ ገባ የሚባል አይደለም ሲሉ ኃላፊው ይጠቁማሉ። አዘዋዋሪዎች በነፍስ ወከፍ የሚመረተውን ወርቅ ከመግዛት ጀምሮ ለጥቁር ገበያው ተጋላጮች መሆናቸውንም ይገልፃሉ። አዘዋዋሪዎቹ ለሕገወጥነት የተጋለጡ በመሆናቸው ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግና መረጃዎች ለማግኘት የሚደረገውን ጥረት በእጀጉ አስቸጋሪ እንዳደረገውም አመልክተዋል።

አቶ ካሚል እንዳሉት፤ በክልሉ በወርቅ ግብይትና ዝውውር ላይ በተደረገ ክትትልና ቁጥጥር 47 በሚሆኑ አዘዋዋሪዎች ላይ በተወሰደ እርምጃ ፈቃዳቸው ተሰርዟል። ለ12 አዘዋዋሪዎች ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል፤ እነዚህ አዘዋዋሪዎች ከሕገወጥ ድርጊታቸው የማይቆጠቡ ከሆነ ደግሞ የማያዳግም እርምጃ ይወሰድባቸዋል።

በክልሉ በወርቅ አምራችነት ሆነ ግብይት ላይ የተሰማሩ አካላት ሕጋዊ ሆኖ መስራት ላይ ችግር እንዳለባቸው ኃላፊው ጠቅሰው፣ ትልቁ ችግር ወርቅ ከተመረተ በኋላ ያለው አሻጥረና የጥቁር ገበያ የዋጋ ጭማሪ ሕገወጥነት እየተሰፋፋ መምጣት መሆኑን አመልክተዋል።

እርምጃ የተወሰደባቸው የውጭ አገር ዜጎች የማዕድን ምርት ላይ ያልተሰማሩ ምንም ሕጋዊነት የሌላቸው እንዴት እንደገቡ እንኳን የማይታወቁ ናቸው የሚሉት ኃላፊው፤ ከአነስተኛ አምራቾች ጋር የሚሰሩ አንዳንድ ሕገወጦች የሉም ማለት አይደለም ይላሉ።

ኃላፊው እንዳሉት፤ በቀጣይም እንደ ክልል በሕጋዊ መንገድ ወርቅ ማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላትን በመቆጣጠር አምራቾች በራሳቸው በቀጥታ ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ የሚያስገቡበት መንገድ በማመቻቸት ሕገወጥነት እንዳይስፋፋ ለማድረግ ይሰራል። አሁን ላይ ብሔራዊ ባንክ የወርቅ ግብይትን የሚፈጽመው በንግድ ባንክ ውክልና ሲሆን፣ ባንኩ በተቻለ መጠን እስከታች ድረስ በመውረድ የግብይት ማዕከል መፍጠር በሚያስችለው ሁኔታ እየሰራ ነው። ይህ ካልሆነ ግን ወርቅ ከቦታ ወደ ቦታ ለማንቀሳቀስ የሚደረግ ሂደት ወርቁን ለሕገወጥነት ተጋላጭ እንዲሆን ያደርጋል።

በክልሉ በወርቅ ላይ የሚፈጸምን ሕገወጥ ተግባር ለመቆጣጠር ግንዛቤ መፍጠር ላይ ትልቅ ሥራ መስራትም ያስፈልጋል። በሕገወጥ ተግባር ላይ ተሰማርተው በሚገኙ አካላት ላይ የማያዳግም እርምጃ በመውሰድ ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሰራል። በክልሉ ከላይ እስከታች ድረስ ያለው የመንግሥት መዋቅር በወርቅ መቆጣጠር ላይ ትኩረት አድርጎ እየተሰራ ይገኛል። ባለው ሥራ ጥሩ ለውጦች እየመጡም ናቸው። ችግሩ ይህ ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግን ይጠይቃል።

አሁን በክልሉ የወርቅ ግብይትን ለመቆጣጣር በርካታ ጥረቶች እየተደረጉ ቢሆንም፣ የሕገወጥነቱ መንገዶችም በዚያ ልክ ብዙ ናቸው። እንደ ክልል ከማምረቻ ቦታ ጀምሮ ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥላል። በፌዴራል ደረጃ ከተቋቋመው ግብረ ኃይል ጋር በጋራ የሚሰሩት ሥራዎችም እንዲሁ ይጠናከራሉ።

ባለፉት ሁለት ዓመታት በነበረው የሰላም ችግር ክልሉ ያለውን የወርቅ አቅም አሟጦ አልተጠቀመም ያሉት ኃላፊው፤ በክልሉ ወርቅ የሚመረተው በአሶሳ ዞን ብቻ እንደነበር ይጠቁማሉ። አሁን በክልሉ በሰፈነው ሰላም በየቦታው እንቅስቃሴ ማድረግ መጀመሩን ጠቅሰው፣ ክልሉ ያለውን የወርቅ አቅም ሁሉ አሟጦ መጠቀም አለበት በሚል እቅድ መያዙን ይናገራሉ። መተከል እና ከማሼ ዞኖች ወርቅ የማምረት ትልቅ አቅም ያላቸው ቦታዎች መሆናቸውን ጠቁመው፤ እየተሻሻለ የመጣውን የጸጥታ ሁኔታ በመጠቀም መሟላት ያለባቸውን ምቹ ሁኔታዎች በማሟላት የወርቅ አምራቶች ወደ ሥራ እንዲገቡ በማድረግ ወርቅ የማምረት አቅምን አሟጦ መጠቀም እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ።

በሌላ በኩል ወደ ሥራ ያልገቡ ኩባንያዎችንም ሆነ አነስተኛ አምራቾች ወደ ሥራ እንዲገቡ በማድረግ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር እንደሚያስፈልግም ነው የገለጹት። ወርቅን የሚገዛው ብሔራዊ ባንክም ወርቅ የሚመረትባቸው አካባቢዎች ድረስ መግዛት የሚችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንደሚጠበቅበት አመልክተዋል። ይህ ሁሉ ከሆነና በክልሉ በኩል የሚደረገው ክትትልና ቁጥጥር ተጠናክሮ እንዲቀጥል ከተደረገ ወርቅን ትርጉም ባለው መልኩ ለአገር ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማዋል ይቻላል ሲሉ ተናግረዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ዓርብ ማታ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ዓርብ የገድ ቀኔ ነው። ዓርብ መጥቶ ሳይቀናኝ ቀርቶ አያውቅም። በረከቶቼ ሁሉ ዓርብ እለት የተዋወኳቸው ናቸው። አያቴ ታዲያ ዓርብን አትወደውም። ዓርብ ምን እንዳደረጋት እንጃ ምንም ይሁን ዛሬ ዓርብ ነው የምትለው ፈሊጥ አላት። እኔን እንኳን ብዙ ጊዜ ዛሬ ዓርብ ነው ደማቅ ልብስ አትልበስ። ዛሬ ዓርብ ነው ወደወንዝ እንዳትወርድ። ዛሬ ዓርብ ነው ከቤት እንዳትወጣ ብላኝ ታውቃለች። ዓርብና አያቴ ለምን በዛ ልክ እንደተጠማመዱ ሳላውቅ አደኩ። አድጌ እንኳን የዓርብ በረከት አልተወኝም።

አንድ ከሰዓት..ጀምበር ወደቤቷ ስታዘግም ያው እንደነገርኳችሁ ዓርብ እለት ነው ከቤት ወጣሁ። ከቤት ወጥቼ ግን አልቀናኝም ገዴ ባልኩት ዓርብ ላይ ወዴትም የማያንቀሳቅስ አንድ አደገኛ የሴት ልጅ ውበት ገጠመኝ። ከቁጥጥሬ ውጪ የሆነ ‹ዋው› የሚል የአድናቆት ድምጽ ከአፌ ሲወጣ ማስቆም አልቻልኩም። ዓርብ ብዙ ዕድሎችን አሳይቶኝ ያውቃል እንደዛሬ አድርጎኝ ግን አያውቅም። አስፓልቱን ስትሻገር ቆሜ ሳያት አስታውሳለሁ። አስፓልቱን ጨርሳ ከፊት ለፊት ካለ ዘመናዊ ካፌ ስትገባ ቆሜ ሳያት ነበር።

ወደገባችበት ካፌ አቀናሁ። ‹ሴት ኃጢያት ናት። እንደ ሴት ልጅ ዓለም ኃጢያት የላትም። ሁሉም ኃጢያት ግን የሚሰረዩት በኃጢያተኛዋ ሴት ነው የሚል ከየት እንደመጣ የማላውቀው ሀሳብ ያቋረጠችውን አስፓልት ሳቋርጥ ተዋሓደኝ። ሀሳብ አለቀቀኝም ‹ሁሉም የወንድ ልጅ ኃጢያት በሴት ልጅ የሚሰረይ ነው። ሴት የወንድ ንስሐው ናት› አለኝ ያው ሀሳብ። አስፓልቱን ጨርሼ የገባችበት ሆቴል ገባሁ። ትንሽ አልፍታኝ ማንም እንዳያያትና እንዳያገኛት በሚመስል ሁናቴ አንድ ሰው ብቻ በምታስቀምጥ ብቸኛ ወንበር ላይ በብቸኝነት ተቀምጣ አገኘኋት። አቀማመጧን ታክኬ በብዙ ነገር እርግጠኛ ሆንኩ። የመጀመሪያው ሰው እንዳልቀጠረች እና እንዳልቀጠራት። ሰው ብትቀጥር ማንም ፈልጎ በማያገኛት ሰዋራ ቦታ ላይ ራሷን አትሰይምም ነበር አልኩ። ቀጥሎ..የሆነ ሩህሩህ እጅ የምትፈልግ መሰለችኝ። አቀማመጧ..አይዞሽ ባይ ክንድ የሚፈልግ መስሎ አዕምሮዬ ውስጥ መጣ። ቀጥሎ.. ቀጥሎ ብዙ አሰብኩ። ያሰብኩት ሁሉ እውነት ከሆነ ሀሁ ላጠና እንደገና ትምህርት ቤት መግባት እንዳለብኝ አመንኩ። ይቺን ቆንጆ ሴት በገመትኩት ግምት ውስጥ እውነት ሆና ካገኘኋት እስካሁን ድረስ ቆንጆ ሴቶችን በሚመለከት የማውቀው ነገር ሁሉ ውሸት ነው ስል ደመደምኩ። የሆነው ሆኖ ፊት ለፊቷ ተቀመጥኩ። እንድታየኝ ሆኜ።

የዛሬ ትልቁ ጉዳዬ ይቺን ሴት መተዋወቅ እንደሚሆን አላጣሁትም። መተዋወቅ ብቻ አይደለም በቀሪ ዘመኔ ሙሉ የምደነቅበትን አጋጣሚ መፍጠር እንዳለብኝ ሲሰማኝ ነበር። የሴት መልክ አይቼ ቃላት ያጣሁበት የመጀመሪያው ቀን በወንድነቴ ውስጥ ተፈጠረ። ከራሴ አልፌ ለብዙ የሰፈር ልጆች የሴትን ልብ የሚቆፍር በውብ ቃላት ደብዳቤ እንዳልጻፍኩ እና በምናገራቸው ውብታም ቃላት ሴቶች በፍቅር እንዳልወደቁልኝ ዛሬ ለዚች ሴት አቅመ ቢስ ሆንኩ። ፍጹምናዋን የምገልጽበት አንደበት አጠረኝ።

ዓርብን ዛሬ ገና ፈራኋት። በልጅነቴ የተዋወኳትን ቅዱስ ዕለት ሰጋኋት። ስትቸረኝ የኖረችውን ዕድል አሳይታ ልትነሳኝ፣ በዚች ሴት ልትቀጣኝ አመሻሽ ላይ ከቤት ያስወጣችኝ መሰለኝ። በመደነቅ አፌን የከፈትኩባቸው፣ በተመስጌን ባዶዬን የሞላሁባቸው ያለፉ ዕድሎቼ ይቺን ሴት የራስ ከማድረግ ጋር አይደለም ከመተዋወቅ ጋር ሲነጻጸሩ እንኳን ኮሰሱብኝ። ፊት ለፊት በደንብ አየኋት። ሞባይሏ ላይ አቀርቅራለች። ቀይ ናት..ምሥራቅ አድማስ ላይ እንዳቅላላች አራስ ጀምበር። ፀሐይን የሚመስል የዓለም አይኖችን ሁሉ የሚያጥበረብር ውበት አላት። ሰማይን የሚያክል ለብዙ ነፍሶች የሚበቃ ሰፊ ሴትነትም። አልተኳኳለችም..ከንፈሯ ላይ ብቻ ቀይዳማ ቀለም ይታየኛል። ሳታየኝ ባቀረቀረችበት ስልኬን ድምፁን አጥፍቼ ፎቶ አነሳኋት። ዝቅ ያለች እንስት፣ ብርሀን የረጨ ስክሪን ላይ አቀርቅራ ስልኬ ላይ ተፈጠረች።

ላወራትና ላናግራት ከየትኛውም ጊዜ በላይ ራሴን አሰናዳሁ። በዛ ዝምታና በዛ ብቸኝነት ውስጥ እንዴት ብዬ መግባት እንዳለብኝ ያሰላሁትን ስሌት ከአንድ እስከ ዩኒቨርስቲ እስከማገር ድረስ አልሞከርኩትም። ሊተወኝ ያልቻለ መጥፎ ባሕሪዬ ሴት ስቀርብ መጀመሪያ የሚመጣልኝ ውሸት ነው። ወደሕይወቴ የመጡ ሁሉም ሴቶች በውሸት ጀምሬ በእውነት የቋጨኋቸው ናቸው። ለመጀመሪያ ጊዜ ይቺን ሴት በእውነት ልቀርባት ልቤ አስገደደኝ። እውነት መልኩን አላውቀውም..። ፊቷ ስቀርብ ምን እንደምላት እንኳን እርግጠኛ አልነበርኩም። እርግጠኛ የሆንኩበት አንድ ነገር ልዋሻት እንደማይገባኝ ነው።

ከሁነኛ ውሸት ወደሁነኛ እውነት መሸጋገር ኪሎማንጃሮን የመውጣት ያክል አንገዳግዶኝ ነበር። ለዚች ሴት የሚሆን ሁነኛ እውነት በዓለም አጣሁ። በውሸትና በእውነት መካከል የሆነ ነገር ትውስ አለኝ። ትውስታዬ እንዳይሰወርብኝ ሰግቼ ወንበሬን ይዤ ወደተቀመጠችበት ሄድኩ። ስታየኝ በትንሹ ደንገጥ ብላ ተረጋጋች።

እንደደረስኩ ‹ጠባቂዎችሽ የሉም? አልኩ ዙሪያዬን እየቃኘሁ።

‹የምን ጠባቂ? ስትል ግራ ለመጋባት ሞከረች። አካሏ ላይ ብቻ አይደለም ድምጽዋም ላይ ብቸኝነት የወደቀባት ሆና አገኘኋት።

‹መቼም ይሄ ውበት ያለጠባቂ ነው የሚንቀሳቀሰው ትይኝና ዓመት እንዳልስቅ› አልኳት።

ሳቀች..የትም ያልተሰማ ውብታም ሳቅ። የቪክቶሪያን ፏፏቴ የሚያስንቅ ደስ የሚል ሳቅ አደመጥኩ። ሳቋ ሌላ ውበቷ ሆኖ አደነዘዘኝ። ማደንዘዣ እንደወጉት ሰው ደነዘዝኩ። በሴት ሳቅ ስደነዝዝ ያ የመጀመሪያዬ ሆነ። ሀይ ስኩል እያለን በሳቋ ብቻ ያፈቀርኳት ወጋታ በዚች ሴት ሳቅ ደበዘዘችብኝ።

‹እስከዛሬ ውበቴን በተመለከተ ከወንድ አፍ ሰምቼው ያሳቀኝ ወሬ አልነበረም› አለች።

‹ለምን? አልኩ ተቻኩዬ። ተቻኩዬ ብቻ አይደለም በችኮላዬ ውስጥ ግራ መጋባትም ነበረበት።

‹ሁሉም ወንዶች የሴትን ልጅ ውበት በተመለከተ አንድ ዕውቀት ብቻ ነው ያላችሁ። እንዲህ እንዳንተ ቆንጆ ነሽ፣ ታምሪያለሽ ብቻ። እኔ ቆንጆ ነሽ ብቻ የሚለኝን ወንድ አልፈልግም። ወደሕይወቴ የሚመጣው ወንድ ሌሎች ወንዶች ያላዩትን የሚያይ እንዲሆን እፈልጋለሁ። አዲስ ነገር ናፋቂ ነኝ› ካለችኝ በኋላ አሳዘንኳት መሰለኝ እንጃ ‹ዛሬ ግን አስቀህኛል እንኳን ደስ አለህ› አለችኝ።

እንደዛሬ የኮራሁበት አጋጣሚ የለም። ስንት ጀብድ የሠራ ወንድነቴ ይቺን ሴት ማሳቅ በመቻሉ የተሰማውን ኩራት የትም አላስተናገደም። እንዴትም ባስብ ወደሕይወቷ መግቢያ ቀዳዳ አጣሁ። ቀላል ሆና የማትቻል ሆነችብኝ። ቀላል ሆኖ አለመቻል ይቻላል?

ቀጥዬ ምን ማለት እንዳለብኝ ያሰብኩትን ማሰብ፣ የተከዝኩትን ትካዜ የትም፣ መቼም፣ ለማንም እንደማልደግመው ባለሙሉ ተስፋ ነበርኩ። ወደልቧ መግቢያ ቀዳዳ አጣሁ። ትንሽዬ የማርያም መንገድ ሻትኩ። በመጨረሻም በሳቋ መግባት እንዳለብኝ አሰብኩ። ዘፍጥረት ታወሰኝ በሔዋን ሳቅ ሞት እንደመጣ። ጊዜ አላጠፋሁም ‹ከዛሬ ጀምሮ ያለምንም ክፍያ ለውበትሽ ዘብ ልቆም ራሴን አዘጋጃለሁ› አልኳት ከተውኩት ውሸት ጋር እየተገናኘሁ።

ከቅድሙ የተለየ መልከ ልውጥ ሳቅ አስተናገድኩ። በአንድ ጉሮሮ የተለያየ ሳቅ? አጀብ አልኩ። አንድ አይነት ሳቅ የላትም። ቅድም የተደነኩበት፣ ልጅነቴን ያስረሳኝ ሳቋ በሌላ ኃይለኛና መልከኛ ሳቅ ተቀይሮ ለሁለተኛ ጊዜ ደነዘዝኩ። ከሳቋ ሌላ ወደዚች ሴት ልብ መግቢያ መንገድ እንደሌለኝ ለብዙኛ ጊዜ እርግጠኛ ሆንኩ።

ጆሮዬ የማይታመን ነገር ሰማ። ‹ደስ ይለኛል› ስትል ሰማሁ። ዓርብ መጥቶ አፍሬ አላውቅም።

ቀጥዬ የተሞላቀቅኩ ይመስለኛል። ዘና ለማለት እየሞከርኩ (በዛ ውበት ፊት ዘና ማለት የማይቻል ከተቻለም በሚሊዮን ዓመታት ውስጥ አንድ ጊዜ እንደሆን የገባኝ እኔ ብቻ ነኝ) ታዲያ ምን አሞላቀቀኝ? እኔጃ! ብቻ ያልገመትኩትን የእሺታ መልስ በመስማቴ እንደሚሆን አታጡትም።

‹ጥበቃዬን ከዛሬ መጀመር እፈልጋለሁ። እናም ዛሬ ማታ ራት ልጋብዝሽ ምኞቴ ነው› ስል ቅደም ተከተሉን ስለመጠበቁ እርግጠኛ ያልሆንኩትን፣ ቀጥሎ ምን እንደምትለኝ ማወቅ አይደለም ለመገመት የማልደፍርበትን ጥያቄ ጠየኳት።

ከአፏ መቼም የማይታመን አንድ እውነት ሰማሁ ‹እንደምኞትህ ይሁን› የሚል። ያን አይነት ምላሽ ስለመስማቴ ለማመን ስንት ደቂቃ ዝም እንዳልኩ አላስታውስም።

ስልክ ተቀያየርን እንደምኞቴ አሪፍ ራት በላን። በነጋታው ‹አዲስ ነገር ያለህ ትመስላለህ። ነፍሴ አዲስ ነገር ላለው ወንድ ቅድሚያ ትሰጣለች..እናም እስከወዲያኛው አብረኸኝ ብትሆን ምኞቴ ነው› አለችኝ።

የሆንኩትን አላስታውስም። የማስታውሰው ነፍሴ በልቤ ውስጥ በደስታ ስትሰቃይ ብቻ ነው። በሕይወቴ ጣይ ያልወጣችበት ወንድነት አልነበረኝም..

# ዓለም አቀፍ

## የካናዳው ዳቦ ቤት ሆነ ብሎ ዋጋ በመጨመሩ 50 ሚሊዮን የካናዳ ዶላር ተቀጣ



ካናዳ ውስጥ ከሚገኙ ዳቦ አምራቾች ቁንጮው ሆነ ብሎ ዋጋ በመጨመሩ የ50 ሚሊዮን የካናዳ ዶላር ቅጣት ተከናንቧል። ካናዳ ብሬድ ባለፈው ረቡዕ ለዓመታት ይህን ጉዳይ ሲፈፅም እንደነበር አምኗል። የካናዳ የገበያ ውድድር ቢሮ ዳቦ ቤቱን ጠርጥሮ ለበርካታ ዓመታት ምርመራ ሲያደርግበት ቆይቷል። ቢሮው ዳቦ ቤቱ ላይ የተጣለው ቅጣት ሲያንስ እንጂ የሚበዛ አይደለም ብሏል።

“የዳቦ ዋጋን ሆነ ብሎ መጨመር፤ ሊያውም የካናዳውያን የዕለት ዕለት ማዕድ የሆነውን ዳቦ? ይህ ትልቅ ወንጀል ነው” የቢሮው ሠራተኛ ማቲው ቦስዌል ናች ይህን ያሉት። “ዋጋ የሚጨምሩ ሌሎች ሰዎችንም እያሳደድን ለሕግ እናቀርባለን” ሲሉ ማስጠንቀቂያ አክለዋል። በኦንታሪዮ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰነደው የክስ መዝገብ እንደሚያሳየው ካናዳ ብሬድ የተሰኘው ድርጅት የዳቦ ዋጋ እንዲንር አድርጓል።

ካናዳ ብሬድ ከተቀናቃኙ ዌስተን ፉድስ ጋር በማበር የሳንድዊችና የቋሊማ እንዲሁም ባለስሙኒው ዳቦ ዋጋ ከፍ አድርጓል። ድርጅቱ ይህን የፈፀመው በፈረንጆቹ 2007 እና 2011 ዓመተ ምሕረት ነው። ቀድሞ ማፕል ሊፍ ፉድስ የተሰኘው ድርጅት ንብረት የነበረው ካናዳ ብሬድ አሁን የሜክሲኮው ግሩፕ ቢምቦ አካል ሆኗል።

ግሩፖ ቢምቦ በለቀቀው መግለጫ ድርጅቱን በ2014 የግል ንብረቱ ሲያደርግ ስለወንጀሉ የሚያውቀው አንዳች ሚስጥር እንደሌለ ገልጧል። “እነሆ አሁን በአዲስ ጥላ ሥር ያለው ካናዳ ብሬድ ለደንበኞቹ መልከና ቁመና ያላነሰው ዳቦ በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ ቆርጦ ተነስቷል። ለካናዳውያን የዳቦ ቅርጫት ከመሆን የሚያግደን የለም” ይላሉ የድርጅቱ ምክትል ፕሬዚዳንት አሊስ ሊ።

ዋጋ እየጨመሩ የካናዳውያንን ኪስ ያራቆቱት የቀድሞ የካናዳ ብሬድ አስተዳዳሪዎች አሁን ድርጅቱን ለቀው ሄደዋል። የገበያ ውድድር ቢሮው ሌሎች ዋጋ የጨመሩ ዳቦ ቤቶች ካሉ የእጃቸውን እንደሚያገኙ ጠቁሟል። የአንድ ዳቦ ዋጋ ማንም ሳያስተውለው በ16 ዓመታት ውስጥ የ1 ዶላር ከሐምሳ ዋጋ ጭማሪ ማምጣቱን ቢሮው ደርሶበታል።

በርካታ ቸርቻሪዎች ዋጋ ጨምራችኋል ተብለው በቢሮው ዓይን ውስጥ ገብተዋል። ነገር ግን አንዱም ጥፋታቸውን አላመኑም። ከሰሞኑ ሥራ የበዛበት የውድድር ቢሮ በቅርቡ የትኛው ‘ሱፐርማርኬት’ የሸቀጥ ዋጋ እንደጨመረ ለሕዝብ ይፋ ሊያደርግ ቋምጧል። ቢሮው ላለፉት ሁለት ዓመታት ምርመራውን ሲከውን መቆየቱን የዘገበው ቢቢሲ ነው።



## ሰሜን ኮሪያ የብሊንከንን የቻይና ጉብኝት "የልመና ጉዞ" ስትል አጣጣለች

ሰሜን ኮሪያ የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን፣ አሜሪካ ከቻይና ጋር ያላትን ውጥረት ለማርገብ በማለም ያደረጉትን ጉብኝት "የልመና ጉዞ" ስትል ተችታለች። ብሊንከን ቻይና ሰሜን ኮሪያ የምታደርገውን የሚሳይል ተኩስ እንድታቆም እንድታግባባት ጠይቀዋል፡፡

ባይደን ወደ ሥልጣን ከመጡ ወዲህ ወሳኝ በተባለው ጉብኝት ወቅት ብሊንከን እና የቻይናው ፕሬዚዳንት ሺ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው ውጥረት ወደ ግጭት እንዳያመራ ግንኙነታቸውን ሰላማዊ ለማድረግ ተስማምተዋል። ከስብሰባው በኋላ ብሊንከን እንደተናገሩት ሰሜን ኮሪያ የምታደርገውን የሚሳይል ተኩስ ቻይና ያላትን መልካም ግንኙነት ተጠቅማ እንድታቆም እንድታግባባት ጠይቀዋል።

ጆንግ ዮንግ ሃክ የተባሉት የሰሜን ኮሪያ የፖለቲካ ተንታኝ በኮሪያ ቴሌቪዥን ቀርበው እንደተናገሩት የብሊንከን የቻይና ጉብኝት በአሜሪካ ላይ ያልተጠበቀ ውድቀት ሊያስከትል የሚችለው ውጥረት እንዲረግብ ለመለመን ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ተንታኙ እንደገለጹት አሜሪካ በቻይና ላይ ያደረሰችው ትንኮሳ የፖሊሲ ውድቀት መሆኑን ያመኑት ዲፕሎማት ጉብኝት የልመና ጉዞ እንጂ ሌላ ሊባል አይችልም ነው ያሉት። አሜሪካ "ጸረ ቻይና ቡድኖችን" በመፍጠር በቀጣናው ለሚፈጠረው ውጥረት ኃላፊነት አለባት ብለዋል።




# አዲስ ዘመን ዓርብ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የማሠልጠኛ ማዕከላት አትሌቲክስ ሻምፒዮና ነገ ይጠናቀቃል

ዓስማየሁ ግዛው

3ኛው የኢትዮጵያ ማሠልጠኛ ማዕከላት የአትሌቲክስ ሻምፒዮና በኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ ከትላንት በስቲያ ጀምሮ እየተካሄደ ይገኛል። ውድድሩ ሦስተኛ ቀኑን ያስቆጠረ ሲሆን በነገው ዕለት ይጠናቀቃል።

ሻምፒዮናው በማሠልጠኛ ማዕከላት ውስጥ ሥልጠናቸውን በመከታተል ላይ ለሚገኙ አትሌቶች የውድድር ዕድል ለመፍጠር ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን፣ በዋናነት ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራትና በማዕከላቱ የሚገኙ አትሌቶች በሚወስዱት ሥልጠና ምን ደረጃ እንዳሉ አቋማቸውን የሚለኩበትም ነው።

በሻምፒዮናው ስድስት የማሠልጠኛ ማዕከላት በተለያዩ የአትሌቲክስ ውድድሮች እየተሳተፉ ሲሆን በርካታ የማጣሪያና የፍፃሜ ፍልሚያዎችን እያስተናገዱ ይገኛሉ። ሀገረ ሰላም፣ ደብረብርሃን፣ ተንታ፣ ቦሬ፣ በቆጂ በሻምፒዮናው እየተሳተፉ የሚገኙ ማሠልጠኛ ማዕከላት ናቸው። ከነዚህ ማሠልጠኛ ማዕከላት የተወጣጡ 160 ወንድና 129 ሴት በድምሩ 289 ታዳጊ አትሌቶች የውድድሩ ተካፋይ ሆነዋል። አትሌቶቹ በአጭር ርቀት፣ መካከለኛ ርቀት፣ ረጅም ርቀትንና በሜዳ ተግባራት ውድድሮች ፉክክር ያደርጋሉ።

በውድድሩ መክፈቻ ዕለት በሁለት ውድድሮች አራት የፍጻሜ ፉክክሮች ተካሂደዋል። እነዚህም የ10ሺ ሜትር ወንድና ሴት እንዲሁም ርዝመት ዝላይ ወንድና ሴት ናቸው። በሁለቱም ፍፃሜዎች ጥሩ ፉክክሮች የተደረጉ ሲሆን የወደፊት ተተኪ አትሌቶችም ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴ



**በሻምፒዮናው ተስፋ ሰጪ ተተኪ አትሌቶች ጠንካራ ፉክክር እያደረጉ ይገኛሉ፣**

አሳይተዋል።

በ10ሺ ሜትር ወንዶች አቤል በቀለ ከተንታ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ 29፡09፡48 በመግባት የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ ሲሆን፣ ኃይሌ ጥጋቡ ከደብረብርሃን 29፡40፡11 በመግባት የብር ሜዳሊያ ወስዷል። አንዳርጋቸው አዳሙ ከተመሳሳይ ማዕከል በ29፡53፡77 የነሐስ ሜዳሊያ ተሸላሚ መሆን ችሏል። በሴቶችም አበበች ተመስገን ከደብረብርሃን፣ አሳመነች ማሙሽ ከቦሬና ኤደን አንተናየሁ ከደብረብርሃን ማሠልጠኛ ከ1ኛ-3ኛ በመውጣት የወርቅ፣ ብርና የነሐስ ሜዳሊያ ተሸላሚ መሆን ችለዋል።

በርዝመት ዝላይ የወንዶች ፍጻሜ ውድድር በጥሶ ቱሞቻ ከሃገረ ሰላም 7 ሜትር በመዝለል አሸናፊ ሲሆን፣ ንጋቱ ዋቶ ከቦሬ ማሰልጠኛ 6.66 ሜትር በመዝለል ሁለተኛ ሆኖ ፈፅሟል። ወንድማገኝ ደገፋ ከተንታ ማሰልጠኛ 6.52 ሜትር በመዝለል የወርቅ የብርና የነሐስ ሜዳለያ ተሸላሚ መሆን ችሏል። ጠንካራ ፉክክርን ያስተናገደው የሴቶች ርዝመት ዝላይ ውድድር በወሎ ዩኒቨርሲቲ የተንታ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ አትሌቶች ከ1ኛ-3ኛ በመውጣት ውድድሩን በበላይነት አጠናቀዋል።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የተሳትፎና ውድድር ዳይሬክተር አቶ አስፋው ዳኜ፣ ፌዴሬሽኑ ከ160ሺ ብር በላይ በጅቶ አትሌቶችን ለማበረታታት ውድድሩን እንደሚያካሂድ ገልፀዋል። አቶ አስፋው በኢትዮጵያ ደረጃ በአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ የሚደገፉ ሰባት የአትሌቲክስ ማሠልጠኛ ማዕከላት እንዳሉ ጠቁመው፣ በውድድሩ ስድስት ማሠልጠኛ ማዕከላት ብቻ እየተሳተፉ እንደሚገኙ ተናግረዋል። በውድድሩ ያልተሳተፈው ብቸኛው ማሠልጠኛ ማዕከል በትግራይ ክልል የሚገኘው የማይጨው ማሠልጠኛ ማዕከል ሲሆን በጦርነት ምክንያት ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ በውድድሩ ሳይካፈል ቀርቷል። ማዕከሉ እራሱን መልሶ በማደራጀትና ሥልጠናዎችን በመጀመር ላይ በመሆኑ የዘንድሮ ውድድር ሊያልፈው መቻሉን አቶ አስፋው ገልፀዋል።

“ወጣት አትሌቶች በማሠልጠኛ ማዕከላት በተገቢው ዕድሜ ተገቢውን ሥልጠና ማግኘት ከቻሉ በአትሌቲክሱ ተተኪ አትሌቶችን ማፍራትና አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ ይቻላል” ያሉት አቶ አስፋው፣ የእድሜ ጉዳይ መጀመር ያለበት ማዕከላት ላይ ሳይሆን ፕሮጀክት ላይ ነው የሚል አስተያየት ሰጥተዋል። በዚህም መሠረት የፕሮጀክት ሰንሰለቱ ተያይዞ ሲሄድ የዕድሜ ማጭበርበር ችግሮች ሊቀረፉ ይችላሉ ባይ ናቸው። ማሠልጠኛ ማዕከላት ላይም ተመሳሳይ ሥራ የሚሠራ ቢሆንም ዋና መሠረቱ ፕሮጀክት በመሆኑ በትኩረት በመሥራት ላይ ይገኛል። ማሠልጠኛ ማዕከላትም የወጣት አትሌቶች መፍለቂያ ናቸው ተብሎ የሚታሰብ በመሆኑ ዕድሜ ላይ የተለመደው ሥራ በቀጣይም ተጠናክሮ እንደሚሠራ አቶ አስፋው ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ለነዚህ ማሠልጠኛ ማዕከላት ሙሉ የትጥቅ ድጋፍን ጨምሮ ለአትሌቶች የላብ መተኪያ እና ለአሠልጣኞች የደሞዝ ክፍያን ይፈፅማል። ማሠልጠኛ ማዕከላቱ ከተለያዩ የፕሮጀክቶችና የክልል ውድድሮች ታዳጊ አትሌቶችን መልምለው በማሠልጠን ለውድድሩ ያቀርባሉ።

ታዳጊ አትሌቶቹ በተለያዩ መድረኮች ውድድሮችን (የኢትዮጵያ ሻምፒዮናና በወጣቶች አቋም መለኪያ) የሚካፈሉ ሲሆን አሁን አሁን ደግሞ ማሠልጠኛ ማዕከላት እርስ በርሳቸው አቋማቸውን የሚለካኩበት ውድድር ተዘጋጅቶላቸው ለ3ኛ ጊዜ በመፎካከር ላይ ናቸው። ይህም የልምድ ልውውጥ በማድረግ ከሌሎች ማዕከላት የሚበልጡበትንና መሥራት ያለባቸውን የቤት ሥራ ለመውሰድ ይረዳቸዋል ተብሎ ይጠበቃል።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ